EVERY CHILD READY @Home

# ክፍል 10

## ወደ ጠፈር መጓዝ

**PK3**



AppleTree


# ክፍል 10
## ወደ ጠፈር መጓዝ


©2021
ሁሉም መብቶች በሕግ የተጠበቁ ናቸዉ። በዚህ የቅጂ መብት ስር ከለላ የተደረገላቸዉን መብቶች ላይ ገደብ ሳያስቀምጥ፣ የዚህ ህትመት የትኛዉም አካል ማባዛት አይቻልም፣ ማከማቸት፣ ወይም በድጋሚ ጥቅም ላይ የሚያዉል ስርዓት ዉስጥ ሊካተት አይችልም፣ ወይም በማንኛዉም መልክ ወይም ሁኔታ(ኤለክትሮኒክ፣ ሜካኒካል፣ ፎቶኮፒ፣ ድምጽ ቅጂ፣ ወይም ሌላ መንገድ) ቀደም ብሎ ከተሰጠ የጽሁፍ ፍቃድ ዉጪ ማስተላለፍ አይቻልም።

አፕል ትሪ ኢንቲቲዩት ፎር ኤዱኬሽን ኤኖቬሽን
1801 ሚሲሲፒ ጎዳና ኤስኢ፣ 3ኛ ፎቅ
ዋሽንግተን፣ ዲሲ 20020

የቅጂ መብት ©2021 ጽሁፍ እና የምስል ገለጻዎች። አፕል ትሪ ኢንስቲቲዩት። ሁሉም መብቶች በህግ የተጠበቁ ናቸዉ።

# የPK3 ክፍል 10 ጠቅላላ ምልከታ






**ውድ ቤተሰቦች፡**

ወደ ክፍል 10፡ ወደ ጠፈር መጓዝ እንኳን በደህና መጡ! በዚህ ክፍል ስር ልጅዎ ስለ ጨረቃ፣ ጠፈር፣ የጠፈር ተመራማሪዎች፣ የመሬት ስበት፣ ጥላዎችና ነጸብራቆች ይማራል።

## ክፍል 10 መጻህፍት




- Counting to 20 in Space በ Beryl Salinger Schmitt
- Space በ Cathryn O'Sullivan
- A Voyage to Space በ Katie Sivinski
- Coyote and Rabbit በ Felicia R. Truong

በተጨማሪም የመጽሀፍ በቅድሚያ በድምጽ የተቀዱ ምንባቦችን ከSparkler መተግበሪያ ላይ "ለአዋቂዎች የቀረቡ ፍንጮች" ወደ ጠፈር መጓዝ ክፍል ስር ማግኘት ይችላሉ!e!

*የECR@Home ተግባሮች የፀሀይ ስርአትን መስራትን እና ስለ መሬት ስበት፣ የጨረቃ ዙሮች፣ የቀን ጊዜ እና የምሽት ጊዜ በተመለከተ ለመማር ምርምር መስራትን ይይዛል። ልጅዎ በተጨማሪም እስከ 10 የሚደርሱ ቁሶችን ይሰራል እንዲሁም ይቆጥራል፣ ከ0-10 ያሉ ቁጥሮችን ለይቶ ያውቃል፣ የቃላት ክፍሎችን ይቀላቅላል፣ ሁለት ክስተቶችን የሚይዙ ታሪኮችን ያዘጋጃል እንዲሁም የችግሮች መፍቻ ዘዴዎችን ይማራል። እነዚህን ተግባሮች ጨረቃ በእያንዳንዱ ምሽት ምን እንደምትመስል በማየትና በመሳል እና መልእክት በሚያዘጋጁበት ወይም የእግር ጉዞ በሚያደርጉበት ወቅት ወደ ጥንብ አንሳ አደን ቁጥር በመሄድ በቀኑ ውስጥ በሙሉ ማካተት ይችላሉ።*

## ክፍል 10 ቃላት

- የጠፈር ተመራማሪ
- የመሬት ስበት
- ጨረቃ
- ፕላኔት
- ነጸብራቅ
- ጥላ
- ጠፈር
- የጠፈር መንኮራኩር
- ጸሃይ



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።


# ሰሙን 1


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# የPK3 ክፍል 10 ሳምንት 1 ጠቅላላ ምልከታ

## ፀሀይና ጨረቃ፣ ቀንና ሌሊት

### በዚህ ሳምንት ልጅዎ፥




በዚህ ሳምንት ልጅዎ ስለ ጨረቃ ዙሮች፣ ቀንና ሌሊት፣ እና የጨረቃ ገሞራዎች ለመማር ምርምሮችን ይሰራል። ልጅዎ በተጨማሪም የቃላት መጀመሪያና የመጨረሻ ድምጾችን ይቀላቅላል፣ ስለ ችግሮች መፍቻ ዘዴዎች ይማራል እንዲሁም እስከ 10 ቁሶችን ይቆጥራል እንዲሁም ያዘጋጃል። እነዚህን ተግባሮች ለማስፋፋት ሰማይ በቀን ውስጥ በተለያዩ ጊዜያት ምን እንደሚመስል ተነጋገሩ እንዲሁም ጠረጴዛ ላይ በምትቀመጡበት ወቅት እንደ ሹካዎች የመሳሰሉ ቁሶችን ይቁጠሩ። እንደ ጨረቃና መዝለያ ዣንጥላ የመሳሰሉ የልጅዎን ስራዎች ለሳምንት 3 በጋራ እንድትጠቀሙባቸው ያስቀምጧቸው።

### ቁልፍ ቃላት




**ጨረቃ**

በመሬት ምህዋር ዙሪያ የምትንቀሳቀስ ክብ ነገር ነች። ምድር በምሽት ሰማይ ላይ ማየት የሚችሉት አንድ ጨረቃ አላት።



**ጠፈር**

ከመሬት ውጭ ያለ የከዋክብትና ፕላኔቶች መገኛ ቦታ ነው



**ጸሃይ**

በቀን ማየት የምንችላት ብርሀን እና ሙቀት የምትሰጠን ኮከብ ነች


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ግንኙነቶችን ይፍጠሩ

በዚህ ሳምንት ስለ ቀንና ሌሊት ይማራሉ። መርሀግብሩን ከመጀመርዎ በፊት የሚመርጡት ቀንን ወይም ሌሊትን ስለመሆኑ እና ለምን እንደሚመርጡ በተመለተ ይጻፉ እንዲሁም ይሳሉ።

ያስቡበት!


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

## STEM: ቁጥሩን ጥራ (0-5)

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ወረቀት፣ ከለሮች**

- ሁለት የተለያዩ ከ0-5 ቁጥሮችን የያዙ የቁጥር ካርዶች ያዘጋጁ። አንዱን ለልጅዎ ይስጡትና ሌላኛውን ይያዙ።
- የቁጥር ካርዱን ያሳዩት። ልጅዎን ቁጥሩን እንዲነግርዎ ይጠይቁት። ልጅዎን ከያዘው ካርድ ላይ ተመሳሳዩን ቁጥር እንዲፈልግ ያድርጉ።
- ሚና ተቀያየሩ። ልጅዎ ካርዱን እንዲያሳይዎ ያድርጉ። እርስዎ ቁጥሩን ይጠሩና ይፈልጋሉ።
- ልጅዎ ከ0-5 ቁጥሮችን ለይቶ ካወቀ ቁጥሮቹ ላይ ከፍ ያለ ቁጥር ይጨምሩ።

የቁጥር ካርዶቹን በዚህ ክፍል ስር በኋላ ላይ ለሚሰራ ስራ ያስቀምጧቸው።

## በግል መማር፡ ከጠፈር ላይ ሆኖ ማየት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡** View from Space/ከጠፈር ላይ ሆኖ ማየት, **ወረቀት፣ ውሀማ ቀለም ጥቅል ወይም ከለሮች**



- ከልጅዎ ጋር ጠፈር ላይ ሆኖ ምድርን ወደ ታች ማየት ምን ይመስላል ብሎ እንደሚያስብ ለመነጋገር ስዕሎቹን ይጠቀሙ።
- ልጅዎን ጠፈር ላይ ሆኖ ምድርን ወደ ታች ማየት ምን ይመስላል ብሎ እንደሚያስብ እንዲስል ያድርጉ።
- ከዚያም **እስኪ ስለ ስዕልህ ንገረኝ! ከጠፈር ላይ ሆነህ ምን ማየት ትችላለህ?** ብለው ይጠይቁት።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሰኞ


PK3 ክፍል 10 ሳምንት 1 ቀን 1

## እውቀት፥ የቃላት ድምጾችን መቀላቀል

- ለልጅዎ **እስኪ ቃላትን እንቀላቅል! የዚህን ቃል መጀመሪያና ቀሪ ድምጾች እቀላቅላለሁ፤ H-at, h-at** ብለው ይነገሩት። ሁለቱን ክፍሎች አንድ ላይ በሚቀላቅሉበት ወቅት በፍጥነት ይድገሙለት። **H-at, hat። ይህንን ሞክር፣ h-at, hat!**
- ከዚያም **አሁን ያንተ ተራ ነው!** ይበሉት ልጅዎን በ-at, c-at (cat), p-at (pat), እና s-at (sat) የሚያበቁ ሌሎች ቃላትን እንዲቀላቅል ያድርጉ።

## ያንብቡ፥ *ጠፈር ላይ እስከ* **20** *መቁጠር*

ጠፈር ላይ እስከ **20** መቁጠር





በሪል ሶሊንገር ሽሚት


**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** *[Counting to 20 in Space/ጠፈር ላይ እስከ 20 መቁጠር]*

- ከልጅዎ ጋር ሆነው መጽሀፉን ያንብቡ።
- ከዚያም **ወደ ጠፈር ብትሄድ ምን ማየት ትፈልጋለህ?** ብለው ይጠይቁት

በተጨማሪም የመጽሀፍ በቅድሚያ በድምጽ የተቀዱ ምንባቦችን ከSparkler መተግበሪያ ላይ "ለአዋቂዎች የቀረቡ ፍንጮች" ወደ ጠፈር መጓዝ ክፍል ስር ማግኘት ይችላሉ!


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።







©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ማክሰኞ



## STEM: ጨረቃ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ [Solar System/የፀሀይ ስርአት](), [Moon/ጨረቃ](), ባትሪ ወይም የስልክ የባትሪ መተግበሪያ፣ ኳስ ወይም እንደ ኳስ የተጠቀለለ ወረቀት ወይም ክብ ፍራፍሬ**

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው የጨረቃ ስዕል ተመልከቱ። ስለ እያንዳንዱ ዙር ይግለጹለት።
- ወደ ጨለማ ክፍል ሂዱ። የጨረቃ መጠን ለምን እንደሚቀየር ለማሳየት ባትሪ ወይም ኳስ ይጠቀሙ። ባትሪውን ኳሱ ላይ ያብሩና መልሰው ያንቀሳቅሱት።
- ከዚያም **ምን ይታይሀል?** ብለው ይጠይቁት። ያብራሩለት። **ብርሀን እንደሚበራበት ቦታ ላይ ተመስርቶ የጨረቃ የተለያዩ ክፍሎችን ማየት ትችላለህ።**




## በግል መማር፥ የምሽት ሰማይን መቀባት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ውሀማ ቀለም ጥቅል ወይም ከለሮች፣ ወረቀት፣ *በአማራጭነት - እንደ ማጣበቂያ፣ ጨው፣ የከዋክብት መስሪያ አንጸባራቂ ወይም ፎይል፣ ደመና መስሪያ የጥጥኳሶች፣ ወዘተ***

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው በምሽት ሰማይ ላይ ምን ማየት እንደሚፈልግ በተመለከተ ተነጋገሩ። ከታብሌት ወይም ስልክ ላይ ስዕል ልትመለከቱ ትችላላችሁ።
- ልጅዎን የምሽት ሰማይ ስዕሉን እንዲቀባ ያድርጉ። ስዕሉ ላይ ከዋክብት ለመስራት ቀለም ሊያንጠባጥብበት ወይም ጨው ሊበትንበት ወይም ደመና ለመስራት የጥጥ ኳስ ሊያስገባበት ይችላል።
- ከዚያም **እስኪ ስለ ምሽት ሰማይህ ንገረኝ! ስዕል ላይ ምን አስቀመጥክ?** ብለው ይጠይቁት


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ማክሰኞ

PK3 ክፍል 10 ሳምንት 1 ቀን 2

## እውቀት፡ ቀንህ እንዴት ነበር?

- ልጅዎን ስለ ቀኑ ይጠይቁት። ልጅዎን ሁለት ክስተቶችን በቅደም ተከተል እንዲነግርዎ ይምሩት።
- ከዚያም **በመጀመሪያ ምን አደረግክ? ቀጥሎስ ምን አደረግክ?** ብለው ይጠይቁት።


## የጆርናል ሙከራ፡ ጨረቃን መጎብኘት


**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ከለሮች፣ እርሳስ፣ የጨረቃን መጎብኘት የጆርናል ገጽ**


- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ስለ ጨረቃ ተነጋገሩ።
- ከዚያም **ጨረቃ ላይ ብትሄድ ምን እንደምታደርግ ልትጽፍና ልትስል ትችላለህ** ብለው ይንገሩት።
- ከዚያም **የጻፍከውና የሳልከው ስለ ምንድን ነው?** ብለው ይጠይቁት።



ስም፡ ________________
ጨረቃን መጎብኘት ብትችሉ እዛ ሄዳችሁ ምን ታደርጉ ነበር?



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።





















©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።





©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

አዲስ ጨረቃ



ክሬሰንት



ግማሽ ጨረቃ



ሙሉ




©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም፥ ________________

ጨረቃን መጎብኘት ብትችሉ እዛ ሄዳችሁ ምን ታደርጉ ነበር?



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ



## **STEM:** የተለያዩ ጨረቃዎች

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ [የተለያዩ ጨረቃዎች/ የተለያዩ ጨረቃዎች](), ከለሮች፣ ለህጻናት ተስማሚ መቀሶች፣ ወረቀት**



- ልጅዎን ጨረቃዎቹን እንዲቆጥራቸው እና ከዚያም ቀለም ቀብቶ ቆርጦ እንዲያወጣቸው ያድርጉ።
- 4 ጨረቃዎች ያስቀምጡ እና ልጅዎን እንዲቆጥራቸው እና ከዚያም ተጓዳኝ ቁጥራቸውን ከቁጥር ካርድ ላይ እንዲፈልግ ይጠይቁት
- ሙከራውን በተለያዩ መጠኖች ደግማችሁ ስሩ።
- *በአማራጭነት - ልጅዎ ቁጥር ሊመርጥና አራት ጨረቃዎች ሊሰራ፣ ሙከራውን ብዙ ጊዜያት ሊደጋግም ይችላል።*

## በግል መማር፥ ጨረቃ መስራት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ [Moon/ጨረቃ](), ውሀማ ቀለም ጥቅል፣ ፎይል ወይም ወረቀት፣ ለህጻናት ተስማሚ መቀሶች፣ *በአማራጭነት - ክር፣ ዱላ ወይም መስቀያ***




- ለልጅዎ ስለ ጨረቃ ዙሮች ይንገሩት። ከዚያም **እስኪ በፎይል** (ወይም በወረቀት) **ጨረቃ ስራ። የትኛውን ዙር መስራት ትፈልጋለህ?** ብለው ይጠይቁት። ልጅዎን ቀለም በመጠቀም ገሞራ እንዲጨምር ያድርጉ።
- ከዚያም **እስኪ ስለ ጨረቃህ ንገረኝ። የትኛውን ዙር መረጥክ?** ብለው ይጠይቁት።
- *በአማራጭነት - ፎይል በመጠቀም ከዋክብት ጨምሩ። ጨረቃና ከዋክብቱን ዱላው ወይም መስቀያው ላይ በክር እሰሯቸው።*


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

## እውቀት፥ እንደ ራስ አድርጎ መረዳት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ወረቀት፣ ከለሮች**


- ለልጅዎ **ችግር በሚያጋጥምበት ወቅት መርዳት የምንችልበት አንደኛው ዘዴ ችግሩን እንደ ራሳችን አድርገን መረዳት ነው። እንደ ራስ አድርጎ መረዳት ማለት ሌላ ሰው ምን እንደሚሰማው ለማወቅ መሞከር ማለት ነው** ብለው ይንገሩት።
- ከዚያም **የሆነን ሰው ስለረዳህበት ጊዜ ልትጽፍና ልትስል ትችላለህ?** ብለው ይጠይቁት። ልጅዎ ጊዜውን ማሰብ ካልቻለ እርስዎ ስላዩት ጊዜ ሊጠቁሙት ይችላሉ። ይህ ምናልባትም ሽክም የተሸከመ ጎረቤት የረዳበት ጊዜ ወይም ወንድም/እህቱ የያዘውን ነገር እንዲያጋራው ሲጠይቀው የሰጠበት ጊዜ ሊሆን ይችላል።
- ስለ ልጅዎ ስዕል በተመለከተ ተነጋገሩ እና ሌላ ሰው የተሰማውን ስሜት እንደ ራሱ ለመረዳት የሞከረበትን ጊዜ ያብራሩለት።

## ያንብቡ፥ *ጠፈር ላይ እስከ **20** መቁጠር*

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** *Counting to 20 in Space/ ጠፈር ላይ እስከ 20 መቁጠር*

- ልጅዎን በምታነቡበት ወቅት ከ1-10 ቁጥሮችን በስም እንዲጠራ ያበረታቱት።
- ከዚያም **እስኪ ከታሪኩ ውስጥ ስለ ሁለት ነገሮች ንገረኝ። መጀመሪያ የተከሰተው የትኛው ነው?** ብለው ይጠይቁት።

ጠፈር ላይ እስከ **20** መቁጠር




በሪል ሶሊንገር ሽሚት


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ



## እስኪ እንንቀሳቀስ፥ ወደ ቁጥር መሄድ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከ0-10 የቁጥር ካርዶች፣ *በአማራጭነት - ሙዚቃ***


- የቁጥር ካርዶቹን በክፍሉ ውስጥ በዘፈቀደ ያስቀምጧቸው።.
- ከልጅዎ ጋር ሆነው ከ0-10 ቁጥሮችን ለዩ። ከዚያም **እኔ ቁጥር እጠራልህ እና አንተ ቁጥሩን ትፈልጋለህ። በክፍሉ ውስጥ በምትንቀሳቀስበት ወቅት እንደ መንኮራኩር መብረር አስመስለህ ተንቀሳቀስ!** ብለው ይንገሩት። ገለጻ ያድርጉለት።
- በጋራ የምትፈልጓቸው የተለያዩ ቁጥሮችን ለመጥራት ተራ ተቀያየሩ።

## አንድ ላይ ሆኖ መማር፥ መፍትሄያችን

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ወረቀት፣ ከለሮች**

- ከልጅዎ ጋር ስለ ችግር ተነጋገሩ፤ ለምሳሌ፡ የጎረቤታችሁ ምግብ/መጠጥ ለማግኘት እርዳታ መፈለግ፣ ለእራት ምን እንደምትሰሩ እርግጠኛ አለመሆን ወይም የአንዳንድ ሰዎች መደበኛ የቤት ውስጥ ስራዎችን ለመስራት ፍላጎት አለመኖር
- ከዚያም **እስኪ ስለ መፍትሄው በጋራ እናስብ። ይህን ችግር እንዴት መፍታት እንችላለን?** ብለው ይጠይቁት። አንድላይ ሆናችሁ ልጅዎ ከመሞከሩ በፊት ሊጽፍና ሊስል ስለሚችለው መፍትሄ ተነጋገሩ።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።




©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሃሙስ



## **STEM:** ቀንና ሌሊት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ባትሪ፣ ኳስ**


- እስኪ **ኳሱን ምድር እና ባትሪውን ፀሀይ እንደሆኑ አድርገን እንውሰድ!** ብለው ይንገሩት። ልጅዎን ባትሪውን እንዲይዝ ያድርጉ። **ፀሀይ በቀን ወቅት ለምድር ብርሀን ትሰጣለች** ብለው ይንገሩት። በቀን ሰአት ስለምትሰሯቸው ነገሮች ተነጋገሩ።
- ኳሱን በጥቂቱ ያዟዙሩ። ከዚያም **አሁን ብርሀን የወጣው በምድር የተለየ ክፍል ላይ ነው። በምሽት ወቅት የሚሆነው እንዲህ ነው** ብለው ይንገሩት። አንድ ላይ ሆናችሁ በምሽትት ስለምትሰሯቸው ነገሮች ተነጋገሩ።

## በግል መማር፥ መዝለያ ጃንጥላ/ፓራሹት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ [Counting to 20 in Space/ ከጠፈር ላይ እስከ 20 መቁጠር፣]() በሚወድቅበት ወቅት የማይሰበር ቀላል ክብደት ያለው ቁስ፤ ለምሳሌ፡ አሻንጉሊት ወይም ኳስ፤ ወረቀት፣ ከለሮች፣ እንደ ስካርፍ፣ ቀላል ፎጣ፣ የፊት ጭምብል የመሳሰሉ ልብሶች**

- ገጽ 32-33ን ያሳዩት እና **የመዝለያ ዣንጥላ የጠፈር ተመራማሪዎችን ቀስ በቀስ እንዲንሳፈፉና ደህንነታቸው ተጠብቆ እንዲወርደ ይረዳቸዋል። አየር የመዝለያ ዣንጥላውን ወደ ላይ ስለሚገፋው ወደ ታች የሚወርደው ቀስ በቀስ ነው** ብለው ይንገሩት።
- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው አሻንጉሊት ከላይ ወደ ታች ይጣሉና በምን ያክል ፍጥነት እንደሚወርድ ተመልከቱ።

ስንለስ አብረኸን ትጓዛለህ**?**
ጸሃይን አልፎ፣ ተወርዋሪ ኮኮቦች፣ እና ጨረቃዎች
ከፈጣሪያቸው ጋር። ፕላኔቶችን አልፎ፣ ጋላክሲዎች፣
አስትሮይዶች፣ ኮንስታሌችኖች። በተጠቀጠቀ ዳመና ውስጥ፣
ከዛም ወደምድራችን ተመልሰን መጥተን ፓራሹቱ ወደ ምድር
በዝግታ ያደርሰናል




- ልጅዎን የመዝለያ ዣንጥላ ዲዛይን እንዲሰራና እንዲስል ያድርጉ።
- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ልብሱን በልጅዎ ዲዛይን ላይ ተመስርታችሁ የመዝለያ ዣንጥላ ለመስራት ተጠቀሙበት። አሻጉሊቱን ደግማችሁ ጣሉ።
- አንድ ላይ ሆናችሁ አሻንጉሊቱ በመዝለያ ዣንጥላ እና ያለ መዝለያ ዣንጥላ እንዴት እንደሚወርድ ተነጋገሩ።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሃሙስ



## እውቀት፥ የቃላት ድምጾችን መቀላቀል

- ለልጅዎ **እስኪ ቃላትን እንቀላቅል! የዚህን ቃል መጀመሪያና ቀሪ ድምጾች እቀላቅላለሁ፤ C-an, c-an** ብለው ይንገሩት። ሁለቱን ክፍሎች አንድ ላይ በሚቀላቅሉበት ወቅት በፍጥነት ይድገሙለት። **C-an, can. ይህንን ሞክር፣ c-an, can!**
- ከዚያም **አሁን ያንተ ተራ ነው!** ይበሉት ልጅዎን በ-an, m-an (man), t-an (dan), እና f-an (fan) የሚያበቁ ሌሎች ቃላትን እንዲቀላቅል ያድርጉ።

## የጆርናል ሙከራ፥ ሰማይ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከለሮች፣ እርሳስ፣ የሰማይ የጆርናል ገጽ**

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው በቀኑ ውስጥ የተለያዩ ጊዜያት (ጠዋት፣ ፀሀይ ሲጠልቅ፣ ምሽት) ሰማይ ስዕሎችን ተመልከቱ። ልጅዎን ስላየው ሰማይ እንዲገልጽልዎ ይጠይቁት።
- ልጅዎን ስለ ሰማይ እንዲጽፍና እንዲስል ያድርጉ።
- ከዚያም **ከቀኑ ውስጥ የምትወደው ጊዜ የትኛው ነው? በዚህ ጊዜ ሰማይ ምን ይመስላል?** ብለው ይጠይቁት


ስም፥ ________________

ከቀኑ ውስጥ እናንተ በእጅጉ በምትወዱት ሰዓት ላይ ሰማዩ ምን እንደሚመስል ስዕል ሳሉ።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም፥ _________________

ከቀኑ ውስጥ እናንተ በእጅጉ በምትወዱት ሰዓት ላይ ሰማዩ ምን እንደሚመስል ስዕል ሳሉ።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።


## **STEM:** ምን ያክል ቁሶች አሉ?

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ እንደ የወረቀት መቆንጠጫዎች ወይም ጠጠሮች ወይም በሸንተረር የተቆራረጡ ወረቀቶች የመሳሰሉ የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች (20)**

- ለልጅዎ 6 የወረቀት መቆንጠጫዎች ያሳዩት። ከዚያም **ስንት መቆንጠጫዎች አሉ?** ብለው ይጠይቁት። እያንዳንዱን የወረቀት መቆንጠጫ ጠቁመው እያሳዩት አብራችሁ ቁጠሩ። ድምሩን ይድገሙለት። **6 የወረቀት መቆንጠጫዎች አሉ!** ብለው ይንገሩት
- ከዚያም ልጅዎን የተለያዩ 6 የወረቀት መቆንጠጫዎች እንዲያዘጋጅ ይጠይቁት።
- ሙከራውን ከ0 እስከ 10 መካከል ባሉ ቁጥሮች ለተጨማሪ ከ2-3 ጊዜያት ደግማችሁ ስሩ። ልጅዎ በተጨማሪም ጥንድ ቁስ ሊያሳይዎና እንዲቆጥሩ ሊጠይቅዎ ይችላል።

## በግል መማር፥ የጨረቃ ገሞራዎች

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ Moon/ጨረቃ, ወረቀት፣ ከለሮች፣ የተለያየ መጠን ያላቸው ኳሶች ወይም ከካልሲ የተሰሩ ኳሶች፣ ወደ ውስጥ ጥልቅ የሆነ የእቃ መያዣ፣ የቆሻሻ ወይም የቡና ቦታዎች**




- በጥልቅ የእቃ መያዣው ውስጥ ቆሻሻ ይጨምሩ
- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው የጨረቃ ገሞራዎች ስዕሎችን ይመልከቱ። ከዚያም **ገሞራዎች እንደ ተወርዋሪ ኮከቦች ያሉ ትላልቅ አለቶች ከጨረቃ ጋር ሲጋጩ ይፈጠራሉ** ብለው ይንገሩት።
- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ኳሶቹን ቆሻሻው ላይ በመጣል ገሞራዎችን ስሩ። የተለያየ መጠን ያላቸው ኳሶች በምትጥሉበት ወቅት ምን እንደሚፈጠር ተነጋገሩ። ኳሶቹን ከተለያየ ከፍታ ላይ በመጣል ተመራመሩ።
- ከዚያም **ስለ ገሞራዎቹ ምን ተመለከትክ? ትልቁን ገሞራ የሰራኸው እንዴት ነው?** ብለው ይጠይቁት።



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# አርብ

PK3 ክፍል 10 ሳምንት 1 ቀን 5

## እውቀት፥ የቃላት ድምጾችን እየቀላቀልን ነው

- ለልጅዎ **እስኪ ቃላትን እንቀላቅል! የዚህን ቃል መጀመሪያና ቀሪ ድምጾች እቀላቅላለሁ፤ P-ig, p-ig** ብለው ይነገሩት። ሁለቱን ክፍሎች አንድ ላይ በሚቀላቅሉበት ወቅት በፍጥነት ይድገሙለት። **P-ig, pig. ይህንን ሞክር፣ p-ig, pig!**
- ከዚያም **አሁን ያንተ ተራ ነው!** ይበሉት ልጅዎን በ-ig, w-ig (wig), d-ig (dig), እና b-ig (big) የሚያበቁ ሌሎች ቃላትን እንዲቀላቅል ያድርጉ።

## ያንብቡ፥ *በጠፈር ላይ እስክ* ***20*** *መቁጠር*

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** *Counting to 20 in Space/ በጠፈር ላይ እስክ 20 መቁጠር*

- ልጅዎን አብራችሁ በምታነቡበት ወቅት ከ1-10 ቁጥሮችን ለይቶ እንዲያወጣ ያድርጉ።
- ከዚያም **ወደ ጠፈር መጓዝ ምን ይመስላል ብለህ ታስባለህ?** ብለው ይጠይቁት።

ጠፈር ላይ እስከ **20** መቁጠር




በሪል ሶሊንገር ሽሚት



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሳምንት 2


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# የPK3 ክፍል 10 ሳምንት 2 ጠቅላላ ምልከታ

## ወደ ጠፈር መጓዝ



### በዚህ ሳምንት ልጅዎ፥


በዚህ ሳምንት ልጅዎ የፀሀይ ስርአትን ይሰራል። ልጅዎ በተጨማሪም የቃላት ክፍሎችን ይቀላቅላል፤ ቃላቱን ለችግር አፈታት እንዴት እንደሚጠቀምባቸው ይማራል እንዲሁም እስከ 10 ቁሶችን ይቆጥራል። ልጅዎን ችግር ሲያጋጥመው የችግር መፍቻ ስትራቴጂዎችን እንዲጠቀም ይርዱት። እንደ የፀሀይ ስርአት የመሳሰሉ የልጅዎን ስራዎች ለሳምንት 3 እንዲጠቀምባቸው ያስቀምጧቸው።

### ቁልፍ ቃላት




**የጠፈር ተመራማሪ**

ወደ ጠፈር የሚጓዝና የሚሰራ ሰው ነው።



**ፕላኔት**

በጠፈር ውስጥ የሚገኝ እንደ ፀሀይ ባለ ኮከብ ዙሪያ የሚዞር ግዙፍ ክብ አካል ነው።



**ጠፈር**

ከመሬት ውጭ ያለ የከዋክብትና ፕላኔቶች መገኛ ቦታ ነው


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ግንኙነቶችን ይፍጠሩ

በዚህ ሳምንት የምንኖርባት ምድርን ጨምሮ በሁሉም ፕላኔቶች የፀሀይ ስርአትን ይሰራሉ። መርሀግብሩን ከመጀመርዎ በፊት ስለሚወዱት ፕላኔት በተመለከተ ይጻፉ እንዲሁም ይሳሉ።

ያስቡበት!


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሰኞ



## STEM: ቁጥሩን ጥራ (6-10)


**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ወረቀት፣ ከለሮች**

- ልጅዎን ሁለት የተለያዩ ከ6-10 ቁጥሮችን የያዙ የቁጥር ካርዶች እንዲያዘጋጅ ይርዱት። አንዱን ለልጅዎ ይስጡትና ሌላኛውን ይያዙ።
- የቁጥር ካርዱን ያሳዩት። ልጅዎን ቁጥሩን እንዲነግርዎ እና ከያዘው ካርድ ላይ ተመሳሳዩን ቁጥር እንዲፈልግ ይጠይቁት።
- ሚና ተቀያየሩ። ልጅዎ ካርዱን እንዲያሳይዎ ያድርጉ። እርስዎ ቁጥሩን ይጠሩና ይፈልጋሉ።
- ልጅዎ ከ6-10 ቁጥሮችን ለይቶ ካወቀ ቁጥሮቹ ላይ ከፍ ያለ ቁጥር ይጨምሩ።

የቁጥር ካርዶቹን በዚህ ክፍል ስር በኋላ ላይ ለሚሰራ ስራ ያስቀምጧቸው።

## በግል መማር፥ በከዋክብት ውስጥ ያሉ ዲዛይኖች

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ Constellations/ የከዋክብት ህብር፣ ወረቀት፣ ውሀማ ቀለም ጥቅል፣ *በአማራጭነት - ጥቁር ወረቀት፣ ማጣበቂያ፣ እንደ ኳስ የተጠቀለለ ፎይል፣ የጌጥ ኳስ ወይም የጥጥ ኳሶች፣ ወዘተ***




- ከልጅዎ ጋር ሆነው የከዋክብት ህብር ስዕሎችን ይመልከቱና ስለ ፓተርኖች ተነጋገሩ። **የከዋክብት ህብር አንድ ላይ ሆነው ፓተርን የሚሰሩ እና ስም ያላቸው ከዋክብቶች ቡድኖች ናቸው** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን ፓተርን ወይም ዲዛይኖች ለመስራት ከዋክብቱን በመቀባት የከዋክብት ህብር እንዲሰራ ያድርጉ።
- *በአማራጭነት - ልጅዎ ለከዋክብት ፎይል፣ የጌጥ ኳሶች ወይም ሌሎች ቁሶችን ሊያስገባ ይችላል።*


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሰኞ



## እውቀት፥ ቃላቶችህን ተጠቀም

- ለልጅዎ **አንዳንድ ጊዜያት እንናደዳለን፣ እንበሳጫለን ወይም ልናለቅስም እንችላለን። እርዳታ ማግኘት ወይም ሌላ ሰው ማናገር ከፈለግን ይህ ሰው ችግራችንን ተረድቶ ሊረዳን እንዲችል ቃላት መጠቀም አለብን** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎ አንድን ችግር ለመፍታት ሊጠቀም ስለሚችላቸው ቃላት ተነጋገሩ፤ ለምሳሌ፡ ልትረዳኝ ትችላለህ፣ ይህን አልወደድኩትም ወይም ልታቆም ትችላለህ።

## ያንብቡ፥ ጠፈር

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** *Space/ጠፈር*

- ከልጅዎ ጋር ሆነው መጽሀፉን ያንብቡ።
- ከዚያም **እስኪ ስለ ሚልኪ ዌይ ጋላክሲ 2 የምታስታውሳቸውን ነገሮች ንገረኝ** ብለው ይጠይቁት። ልጅዎ እርዳታ ከፈለገ መጽሀፉን እንዲያይ ይንገሩት።




በተጨማሪም የመጽሀፍ በቅድሚያ በድምጽ የተቀዱ ምንባቦችን ከSparkler መተግበሪያ ላይ "ለአዋቂዎች የቀረቡ ፍንጮች" ወደ ጠፈር መጓዝ ክፍል ስር ማግኘት ይችላሉ!



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።



ኡርሳ ሜጀር



ጀሚኒ



ካኒስ ሜጀር




ላይራ


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ማክሰኞ



## STEM: የፀሀይ ስርዐት ክፍል 1





**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ Solar System/ የፀሀይ ስርዐት, ወረቀት (ቁርጥራጭ ወረቀት ሊሆን ይችላል)፣ ውሀማ ቀለም ጥቅል ወይም የመጫወቻ ሊጥ ወይም በመጫወቻ ሊጥ የተዘጋጀ ምግብ,** ***በአማራጭነት - ፎይል ወይም እንደ ከዋክብት የመሳሰሉ ተጨማሪ ባህሪያት መስሪያ ሌሎች የማስዋቢያ ቁሳቁሶች***

- ከልጅዎ ጋር ሆነው ስለ ፀሀይ ስርአት እና ፕላኔቶች ተነጋገሩ። ስዕሎቹን አንድ ላይ ሆናችሁ ተመልከቱ።
- አንድ ላይ ሆናችሁ ወረቀት በማጣጠፍ እና እያንዳንዱን ቀለም በመቀባት ፀሀይና ፕላኔቶችን ስሩ። ወይም የመጫወቻ ሊጥ መጠቀም ትችላላችሁ!

የፀሀይ ስርአቱን እንዲደርቅ ያድርጉና ለቀን 9 ያስቀምጡት።

## በግል መማር፥ ጓደኛዬ ማጋራት አይፈልግም



**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ Friends Puppets/ የጓደኛሞች የቤት ውሻ አሻንጉሊቶች, ከለሮች፣ ለህጻናት ተስማሚ መቀሶች፣ ዱላዎች ወይም የተቀረጹ ዱላዎች ወይም ረጅም እጄታ ያላቸው ማንኪያዎች፣ ወዘተ፣ ማጣበቂያ፣ ትንሽ አሻንጉሊት፣** ***በአማራራነት - አሻንጉሊት ውሾቹን ቆርጠው ከማውጣትዎ በፊት ካርቶን ላይ ያጣብቋቸው***

- ከልጅዎ ጋር ሆነው ጓደኛው አሻንጉሊቱን ማጋራት የማይፈልግ ከሆነ ምን እንደሚያደርግ በተመለከተ ተነጋገሩ። ተራውን ሊጠብቅ፣ ጓደኛውን አሻንጉሊቱን እንዲሸጥለት ሊጠይቅ ወይም ጓደኛው ተጫውቶ እስከሚያበቃ ድረስ ሊጠብቅ ይችላል።
- ልጅዎን አሻንጉሊት ውሾቹን ቆርጦ እንዲያወጣቸው ያድርጉ። አሻንጉሊት ውሾቹን ዱላዎቹ ላይ ያጣብቋቸውና ልጅዎን ጓደኛው ለማጋራት ፍቃደኛ ባይሆን ምን እንደሚያደርግ ሚና እንዲጫወት ያድርጉ።
- ከዚያም **ጓደኛህ ማጋራት ባይፈልግ አሻንጉሊት ውሾችህ ምን ይወስኑ ነበር?** ብለው ይጠይቁት።
- አሻንጉሊት ውሾቹን በዚህ ክፍል ውስጥ በሙሉ ለመጠቀም ያስቀምጧቸው


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ማክሰኞ



## እውቀት፥ ታሪካችን

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ወረቀት፣ ከለሮች**

- ለልጅዎ ቀላል ሁለት ክስተቶችን የያዘ ታሪክ ምሳሌ ይንገሩት። እንደ **እኔ (ወይም እኛ) አንድ ጊዜ … እና ከዚያም** … አይነት ምሳሌ ይስጡት።
- ልጅዎ እርዳታ የሚያስፈልገው ከሆነ **እስኪ እኛ …. ጊዜ ንገረኝ** እና **እስኪ ስለተከሰቱ ስለ ሁለት ነገሮች ንገረኝ** ይበሉት።
- **ያ ጥሩ ታሪክ ነበር!** ይበሉት።

## የጆርናል ሙከራ፥ የኮከብ አጥኚ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከለሮች፣ እርሳስ፣ የኮከብ አጥኚ የጆርናል ገጽ**

- ከልጅዎ ጋር ስለ ከዋክብት አጥኚዎችና ስለ ስራቸው ተነጋገሩ። **የኮከብ አጥኚዎች እስደ ከዋክብትና ፕላኔቶች ያሉ በጠፈር ላይ የሚገኙ ነገሮችን የሚያጠኑ ሳይንቲስቶች ናቸው** ብለው ይንገሩት።
- ከልጅዎ ጋር የኮከብ አጥኚ የመሆን ፍላጎት እንዳለው ወይም እንደሌለው በተመለከተ ይነጋገሩ።


ስም፡ ___________________

የስነ ከዋክብት ተመራማሪ መሆን ይፈልጋሉ? ለምን መሆን ይፈልጋሉ ወይስ ለምን መሆን አይፈልጉም?


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# በመጫወቻ ሊጥ የሚደረግ የምግብ ዝግጅት

1 ኩባያ ዱቄት

2 የሻይ ማንኪያ የላመ ክሬም

1/3ኛ ኩባያ ጨው

1 ኩባያ ውሀ

1 የሻይ ማንኪያ የአትክልት ዘይት

የመረጡት አይነት የምግብ ማቅለሚያ

1. ዱቄቱን፣ የላመውን ክሬም እና ጨዉን የምግብ ማብሰያ ድስት ውስጥ ይክተቱ።
2. በምግብ ማብሰያ ድስቱ ውስጥ ውሀና የአትክልት ዘይት ይጨምሩ። ውህዱን በመካከለኛ/አነስተኛ ሙቀት ይቀላቅሉ።
3. ውህዱ መወፈር ከመጀመሩ በፊት የምግብ ማቅለሚያውን ይጨምሩበት።
4. የድስቱ የስረኛው ክፍል ላይ እንዳይይዝ እና እንዳይጋገር ማማሰልዎን ይቀጥሉ።
5. ለጨዋታ ከማዋልዎ በፊት የመጫወቻ ሊጡ እንዲቀዘቅዝ ያድርጉ። ሊጡን አየር በማያስገባ መያዣ ውስጥ ያስቀምጡት።








©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።










©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም፥ ________________

የስነ ከዋክብት ተመራማሪ መሆን ይፈልጋሉ? ለምን መሆን ይፈልጋሉ ወይስ ለምን መሆን አይፈልጉም?


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ




## STEM: ስብስብ ስራ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ 10 ተመሳሳይ ቁሳቁሶች፤ ለምሳሌ 10 ሳንቲሞች ወይም 10 ከለሮች**

- **እስኪ የነገሮች ስብስብ ወይም ቡድን እንስራ። ስብስብህን የምትሰራባቸው ብዙ ቁሶችን እነግርሀለሁ** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን ስብስቦችን ለመስራት ቁሶቹን እንዲቆጥር በማድረግ ከ1-10 የተለያዩ መጠኖች ይስጡት።
- ልጅዎ ስብስብ የሚሰሩባቸው ቁጥሮችን እንዲሰጥዎ ሚናችሁን ተቀያየሩ።

## በግል መማር፥ የጠፈር መገጣጠም

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** [Space Puzzle/ የጠፈር መገጣጠም](), **ከለሮች፣ ለህጻናት ተስማሚ መቀሶች፣ *በአማራጭነት - ቁርጥራጮቹን ከመቀባትዎና ቆርጠው ከማውጣትዎ በፊት ካርቶን ላይ ያጣብቋቸው***




- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ከቁርጥራጮቹ በታች ያሉትን ቁጥሮች ተመልከቱ
- ልጅዎ ቁርጥራጮቹን እንዲቀባ፣ ቆርጦ እንዲያወጣ እና ከዚያም ቁርጥራጮቹን ከ1-10 በቅደም ተከተል እንዲያስቀምጣቸው ያድርጉ።
- ለሙከራ ልጅዎን የተለያዩ ቁጥሮችን ጠቁሞ እንዲያሳይዎ ይጠይቁት


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ

PK3 ክፍል 10 ሳምንት 2 ቀን 8

## እውቀት፥ እስኪ ስለ ጠፈር እንነጋገር

- ከልጅዎ ጋር አብረው ሆነው ስለ ጠፈር በተመለከተ ምን እየተማረ እንደሆነ ይነጋገሩ።
- **በጠፈር ውስጥ ምን ይገኛል?**
- **ጨረቃ ላይ መኖር ምን ሊመስል ይችላል ብለህ ታስባለህ?**
- **ሰዎች ጠፈር ላይ መኖር የማይችሉት ለምንድን ነው?** ብለው ይጠይቁት
- የሀሳብ መለዋወጫ ውይይት ለማድረግ ሞክሩ።

## ያንብቡ፥ *ጠፈር*

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** *Space/ጠፈር*

- ከልጅዎ ጋር ሆነው ያንብቡ።
- ከዚያም **ሙዚየም ውስጥ ምን ተጨማሪ ነገሮች ይኖራሉ ብለህ ታስባለህ?** ብለው ይጠይቁት
- ስለ አየር እና የጠፈር ሙዚየሞች እና የፕላኔት ጥናቶች በተመለከተ ከመጽሀፍ ወይም ከስልክ ወይም ታብሌት ላይ ተጨማሪ መረጃ ተመልከቱ።





©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ



## እስኪ እንንቀሳቀስ፥ እየቆጠርክ መወርወር

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከ0-10 የቁጥር ካርዶች፣ 10 ኳሶች (እንደ ኳስ የተጠቀለለ ወረቀት ወይም ካልሲዎች)፣ የእቃ መያዣ**


- ልጅዎን የቁጥር ካርድ እንዲያነሳና ቁጥር እንዲጠራ ያድርጉ። ብዙ ኳሶችን የእቃ መያዣው ውስጥ እያሽከረከረ እንዲከት ያድርጉ።
- ተራ እየተቀያየራችሁ ብዙ ጊዜያት ደግማችሁ ስሩ።
- *በአማራጭነት - የቁጥር ካርድ አንሱ እና በምትቆጥሩበት ወቅት ኳስ በዛ ቁጥር ልክ ወደ ኋላና ወደፊት ወርውሩ።*

## አንድ ላይ ሆኖ መማር፥ የጠፈር ካምፕ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ካምፕ አስመስሎ ለመስራት የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች፤ ምሳ፡ ድንኳን መስሪያ ወረቀቶች ወይም ፎጣ፣ የጠፈር ተመራማሪ ልብስ፣ ቴሌስኮፖች መስሪያ የተጠቀለለ ሶፍት፣ ማቆያ ምግቦች**

- ለልጅዎ **እስኪ አዲስ ፕላኔት ላይ እንዳረፍን እና ካምፕ መስራት እንደሚያስፈልገን አድርገን እንተውን** ይበሉት። **ድንኳናችንን ለመስራት ምን መጠቀም ያስፈልገናል?** ብለው ይጠይቁት።
- በጋራ የማመን ስርአት አከናውኑ! ድንኳን በመስራት፣ ስለ አዲስ ፕላኔት በማጥናት እና አንድ ላይ ሆናችሁ የጠፈር ላይ ምግብ በመስራት ተዝናኑ።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።






©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

PK3 ክፍል 10 ሳምንት 2 ቀን 9

## STEM: የፀሀይ ስርአት ክፍል 2

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** Solar System/ የፀሀይ ስርአት, **በቀን 7 የተሰሩ ፕላኔቶችና ፀሀይ፣ ካርቶን ወይም መስቀያ፣ ችንጋ፣ ማጣበቂያ**

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ስለሰራቸው ፕላኔቶችና እንዴት አንድ ላይ እንደሚያደርጋቸው በተመለከተ ተነጋገሩ።
- ልጅዎን በእያንዳንዱ ፕላኔት ዙሪያ ቺንጋ እንዲያስርና ቺንጋውን ካርቶን ወይም መስቀያ ላይ እንዲያያይዘው ያድርጉ። ከዚያም ለመዝናናት የጸሀይ ስርአትን ስቀሉ!





የጸሀይ ስርአቱን በሳምንት 3 በጋራ በአየርና የጠፈር ሙዚየም ላይ በምትጫወቱበት ወቅት ለመጠቀም ያስቀምጡት።

## በግል መማር፥ ሌሎችን ጨምሮ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ በቀን 7 የተሰሩት** Friends Puppets/ የጓደኛሞች አሻንጉሊት ውሾች

- ለልጅዎ **እንደ ራስ አድርጎ መረዳት ማለት የሌሎች ሰዎችን ስሜት መረዳት ማለት ነው። እንደ ራሳችን አድርገን መረዳታችን ማሳየት የምንችልበት አንዱ ዘዴ ሌሎች ሰዎችን የብቸኝነተት ስሜት ከተሰማቸውና ለብቻቸው ከተተዉ ከእኛ ጋር እንዲጫወቱ መጋበዝ ነው** ብለው ይንገሩት። **ከእኔ ጋር ልትጫወት ትችላለህ?** ሊሉት ይችላሉ።
- ልጅዎን ሌሎች አብረውት እንዲጫወቱ ለመጋበዝ አሻንጉሊት ውሾቹን እንዲጠቀም ያድርጉ።
- ከዚያም **ጓደኛህ አብሮህ እንዲጫወት ስትጋብዘው ምን ስሜት ተሰማው?** ብለው ይጠይቁት




©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሃሙስ

PK3 ክፍል 10 ሳምንት 2 ቀን 9

## እውቀት፥ እስኪ አስመስለህ ተውን

- ለልጅዎ **እኔ አንድ ቃል እነግርሀለሁ፤ ከዚያም ቃሉ ምን ማለት እንደሆነ አብረን እንተውናለን** ብለው ይንገሩት።
- ከጭብጥ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ቃላት ይጠቀሙ፤ ምሳሌ፡ የጠፈር አጥኚ (የጠፈር ልብስ ለመልበስ መሞከር)፣ ኮከብ (በጣቶችዎ እን ኮከብ ማብለጭለጭና ወደ ሰማይ መጠቆም)፣ ሮኬት (የሚበሩ አስመስለው ይተውኑ)።
- ልጅዎ ቃል እንዲጠቁሙዎ ሚናችሁን ተቀያየሩ።

## የጆርናል ሙከራ፥ ፕላኔት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከለሮች፣ እርሳስ፣** [Solar System/የፀሀይ ስርዐት](), **የፕላኔት የጆርናል ገጽ**

- ከልጅዎ ጋር አብረው ሆነው የጸሀይ ስርአት ስዕሎችን ተመልከቱ እና ስለተለያዩ ፕላኔቶች ተነጋገሩ። ተጨማሪ መረጃ ከስልክ ወይም ታብሌት ላይ ማየት ትችላላችሁ።
- ልጅዎን መኖር ስለሚፈልግበት ፕላኔት እንዲጽፍነና እንዲስል ያድርጉ።
- ከዚያም **መኖር የምትፈልገው የትኛው ፕላኔት ላይ ነው? ለምን?** ብለው ይጠይቁት።


ስም፥ ___________________

በሌላ ፕላኔት መኖር ቢችሉ ኖሮ ሊኖሩበት ስለሚፈልጉት ፕላኔት ጻፉ፣ ስዕልም ስሩ።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም፥ ________________

በሌላ ፕላኔት መኖር ቢችሉ ኖሮ ሊኖሩበት ስለሚፈልጉት ፕላኔት ጻፉ፣ ስዕልም ስሩ።



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# አርብ

PK3 ክፍል 10 ሳምንት 2 ቀን 10

## STEM: የፕላኔት ስብስቦች

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** [Planet Sets/ የፕላኔት ስብስቦች](), **ከለሮች፣ ለህጻናት ተስማሚ መቀሶች፣ ከ0-10 የቁጥር ካርዶች**




- ልጅዎን ፕላኔቶቹን እንዲቆጥራቸውና ቀለም እንዲቀባቸው ከዚያም ቆርጦ እንዲያወጣቸው ያድርጉ።
- 5 ፕላኔት ያስቀምጡና ልጅዎን እንዲቆጥራቸው እና ከዚያም ከብዛታቸው ጋር ተመሳሳይ የቁጥር ካርድ (5) እንዲፈልግ ይጠይቁት።
- ሙከራውን በተለያዩ መጠኖች ደጋግማችሁ ስሩ
- *በአማራጭነት - ልጅዎ ቁጥር ሊመርጥና የፕላኔቶች ስብስብ ሊሰራ ይችላል። ብዙ ጊዜ ደጋግማችሁ ስሩ።*

የቁጥር ካርዶቹን በዚህ ክፍል ውስጥ በሙሉ ለመጠቀም ያስቀምጧው።

## በግል መማር፥ የኔ ፕላኔት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** [Solar System/ የፀሀይ ስርአት](), **ወረቀት፣ ውሀማ ቀለም ጥቅል ወይም ከለሮች፣ የመጫወቻ ሊጥ ወይም** [በመጫወቻ ሊጥ የተዘጋጀ ምግብ]()



በመጫወቻ ሊጥ የሚደረግ የምግብ ዝግጅት

1 ኩባያ ዱቄት

2 የሻይ ማንኪያ የላመ ከሬም

1/3ኛ ኩባያ ጨው

1 ኩባያ ውሀ

1 የሻይ ማንኪያ የአትክልት ዘይት

የመረጡት አይነት የምግብ ማቅለሚያ

1. ዱቄቱን፣ የላመውን ከሬም እና ጨዉን የምግብ ማብሰያ ድስት ውስጥ ይከተቱ።
2. በምግብ ማብሰያ ድስቱ ውስጥ ውህና የአትክልት ዘይት ይጨምሩ። ውህዱን በመካከለኛ/አነስተኛ ሙቀት ይቀላቅሉ።
3. ውህዱ መወፈር ከመጀመሩ በፊት የምግብ ማቅለሚያውን ይጨምሩበት።
4. የድስቱ የስረኛው ክፍል ላይ እንዳይይዝ እና እንዳይጋገር ማማሰልዎን ይቀጥሉ።
5. ለጨዋታ ከማዋልዎ በፊት የመጫወቻ ሊጡ እንዲቀዘቅዝ ያድርጉ። ሊጡን አየር በማያስገባ መያዣ ውስጥ ያስቀምጡት።

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ስለ ፕላኔት ባህሪያት ተነጋገሩ። ሳተርን የበረዶና አለት ቀለበቶች አሏት። ጁፒተር ብዙ ጨረቃዎች አሏት። **የኛ ፕላኔት ምድር ምን ልዩ ባህሪ አላት (ምድራችን ተክሎችና እንስሳት፣ የምንጠጣው ውሀ፣ የምንተነፍሰው አየር አላት)** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን በመጫወቻ ሊጥ ፕላኔት እንዲሰራና ቀለም እንዲቀባው ይፍቀዱለት።
- ከዚያም **እስኪ ስለ ፕላኔትህ ንገረኝ! ፕላኔትህ ምን ልዩ ነገሮችን ይዟል? በፕላኔትህ ላይ ማንኛውም በህይወት የሚኖር ነገር አለ?** ብለው ይጠይቁት


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# አርብ

PK3 ክፍል 10 ሳምንት 2 ቀን 10

## እውቀት፥ የቃላት ድምጾችን መቀላቀል እችላለሁ

- ለልጅዎ **እስኪ ቃላትን እንቀላቅል! የዚህን ቃል መጀመሪያና ቀሪ ድምጾች እቀላቅላለሁ፤** **H-at, h-at** ብለው ይንገሩት። ሁለቱን ክፍሎች አንድ ላይ በሚቀላቅሉበት ወቅት በፍጥነት ይድገሙለት። **H-at, hat። ሞክር፤ h-at, hat!**
- ከዚያም **አሁን ያንተ ተራ ነው!** ይበሉት። ልጅዎን c-up (cup), j-ump (jump), እና p-et (pet) የሚሉትን ቃላት እንዲቀላቅል ያድርጉ።


## ያንብቡ፥ *ጠፈር*

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** *[Space/ጠፈር]*




- ከልጅዎ ጋር ሆነው መጽሀፉን ያንብቡ።
- ከዚያም **በቴሌስኮፕ ውስጥ ብትመለከት ምን ማየት ትፈልጋለህ?** ብለው ይጠይቁት።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።




©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሳምንት 3


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# የPK3 ክፍል 10 የሳምንት 3 ጠቅላላ ምልከታ

## ስለ የጠፈር ተመራማሪዎች በተመለከተ

### በዚህ ሳምንት ልጅዎ፥

በዚህ ሳምንት ልጅዎ አለም አቀፍ የጠፈር ምርምር ጠጣቢያ ይጎነባል እንዲሁም ስለ መሬት ስበት ይመራመራል። ልጅዎ በተጨማሪም ሁለት ክስተቶችን የያዘ ታሪክ ያዘጋጃል፣ የቃላት ክፍሎችን ይቀላቅላል፣ ስለ እራሱና ሌሎች ሰዎች መሬት ላይ ማረፍ ይማራል፣ ስለ ጠፈር ተመራማሪዎች ይማራል፣ የጠፈር ጎጆ ዲዛይን ይሰራል እንዲሁም ቁጥሮችን ይፈልጋል። ልጅዎን የሰራተኞች የደንብ ልብሶችን ጠቁመው በማሳየት ሰዎች ስራዎቻቸውን የሚሰሩባቸውን ልዩ ልብሶች እንደሚለብሱ እንዲገነዘብ ይርዱት።



### ቁልፍ ቃላት




## የጠፈር ተመራማሪ

ወደ ጠፈር የሚጓዝና የሚሰራ ሰው ነው።



## የመሬት ስበት

አንድን ነገር መሬት ላይ እንዲወድቅ የያደርግ ወይም ወደ ሌላ ፕላኔት እንዲሳብ የሚያደርግ ሀይል ነው።



## የጠፈር መንኮራኩር

ወደ ጠፈር ላይ ለመሄድና መሬት ላይ ለመመለስ ጥቅም ላይ የሚውል ተሽከርካሪ ነው


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ግንኙነቶችን ይፍጠሩ

በዚህ ሳምንት ወደ ጠፈር ስለሚጓዙ የጠፈር ተመራማሪዎች ይማራሉ። መርሀግብሩን ከመጀመርዎ በፊት ወዴት መጓዝ እንደሚፈልጉ በተመለከተ ይጻፉ እንዲሁም ይሳሉ።

ያስቡበት!



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሰኞ



## **STEM:** የኮከብ ስብስቦች

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** Star Sets/የኮከብ ስብስቦች**, ከለሮች፣ ለህጻናት ተስማሚ መቀሶች፣ ከ0-10 የቁጥር ካርዶች**



- ልጅዎን ኮከቦቹን እንዲቆጥራቸውና ቀለም እንዲቀባቸው ከዚያም ቆርጦ እንዲያወጣቸው ያድርጉ።
- 8 ኮከቦች ያስቀምጡና ልጅዎን እንዲቆጥራቸው እና ከዚያም ከብዛታቸው ጋር ተመሳሳይ የቁጥር ካርድ (8) እንዲፈልግ ይጠይቁት።
- ሙከራውን በተለያዩ መጠኖች ደጋግማችሁ ስሩ
- *በአማራጭነት - ልጅዎ ቁጥር ሊመርጥና የኮከቦች ስብስብ ሊሰራ ይችላል። ብዙ ጊዜ ደጋግማችሁ ስሩ።*

የቁጥር ካርዶቹን በዚህ ክፍል ውስጥ በሙሉ ለመጠቀም ያስቀምጧቸው።

## በግል መማር፥ በጠፈር ላይ የራሴን ስዕል መሳል/መቀባት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ውሀማ ቀለም ጥቅል ወይም ከለሮች፣ ወረቀት**

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ወደ ጠፈር ቢጓዝ ምን እንደሚያደርግ ተነጋገሩ።
- ልጅዎን ጠፈር ላይ ሆኖ የራሱን ስዕል እንዲስል ያድርጉ።
- ከዚያም **እስኪ ስለ ስዕልህ ንገረኝ! ጠፈር ላይ ሆነህ ምን ታደርጋለህ?** ብለው ይጠይቁት


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሰኞ




## እውቀት፦ ታሪክህ ምንድን ነው?

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፦ ወረቀት፣ ከለሮች**

- ልጅዎን በዚህ ሳምንት ስለተከሰተ ስለሆነ ነገር የተመለከተ ታሪክ እንዲጽፍ ያድርጉ። ልጅዎን በታሪኩ ውስጥ ስለ ሁለት ክስተቶች እንዲያካትት ያበረታቱት።
- ከዚያም **እስኪ ስለ ታሪክህ ንገረኝ! ታሪኩን መተወንም ትችላለህ** ብለው ይጠይቁት።

## ያንብቡ፦ ወደ ጠፈር የሚደረግ ጉዞ

ኬቲ ሲቪንስኪ
ሰዐሊ፦ ጆይስ ዩ





ወደ ጠፈር የሚደረግ ጉዞ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፦** *A Voyage to Space/ወደ ጠፈር የሚደረግ ጉዞ*

- ከልጅዎ ጋር መጽሀፉን አብራችሁ አንብቡ። ልጅዎ በሚጓዝበት ወቅት በገጽ 13 ላይ ያሉትን ቁጥሮች ያሳዩት እና ቁጥሮቹን አንድ ላይ ሆናችሁ ጥሯቸው!
- ከዚያም **ወደ ጠፈር መሄድ ትፈልጋለህ? ለምን ወይም ካልሆነም ለምን?** ብለው ይጠይቁት

በተጨማሪም የመጽሀፉን በቅድሚያ በድምጽ የተቀዱ ምንባቦችን ከSparkler መተግበሪያ ላይ “ለአዋቂዎች የቀረቡ ፍንጮች” ወደ ጠፈር መጓዝ ክፍል ስር ማግኘት ይችላሉ!


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።




©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ማክሰኞ



## **STEM:** አለም አቀፍ የጠፈር ምርምር ጣቢያ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** [International Space Station/አለም አቀፍ የጠፈር ምርምር ጣቢያ](), **ወረቀት፣ ከለሮች፣ እንደ ጥቅል ሶፍት፣ ትናንሽ የእቃ መያዣዎች የመሳሰሉ በድጋሚ ጥቅም ላይ የሚውሉ ቁሶች ወይም የመጫወቻ ሊጥ ወይም** [በመጫወቻ ሊጥ የተዘጋጀ ምግብ]()






- ከልጅዎ ጋር ሆነው ስለ አለም አቀፍ የጠፈር ምርምር ጣቢያና ሳተላይቶች ተነጋገሩ።
- **አለም አቀፍ የጠፈር ምርምር ጣቢያ በጠፈር ላይ የጠፈር ተመራማሪዎች የሚኖሩበት ቦታ ነው። ሳተላይቶች ደግሞ ወደ ምርድ እንደ ቲቪ ማየት እና ኢንተርኔት መጠቀም የመሳሰሉ ነገሮችን ለመስራት የሚያስችሉንን ሲግናሎች/ሞገዶች ይልካሉ** ብለው ይንገሩት።
- አንድ ላይ ሆናችሁ የሳተላይት ዲዛይን አዘጋጁና ሳተላይቱን በቁሳቁሶቹ ስሩ።

## በግል መማር፥ የጠፈር ተመራማሪ ብሆን ኖሮ

ኬቲ ሲቪንስኪ
ሰዐሊ፥ ጆይስ ዩ




ወደ ጠፈር የሚደረግ ጉዞ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ወረቀት፣ ከለሮች,** [*A Voyage to Space/ወደ ጠፈር የሚደረግ ጉዞ*]()

- ልጅዎን የጠፈር ተመራማሪ ቢሆን ምን እነደሚያደርግ ይጠይቁት። መጽሀፉን እንዲያይ ሊመሩት ይችላሉ። ልጅዎ ስለሚያደርገው ነገር እንዲጽፍና እንዲስል ያድርጉ።
- ከዚያም **የጠፈር ተመራማሪ ብትሆን ምን ታደርጋለህ?** ብለው ይጠይቁት።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ማክሰኞ



## እውቀት፥ እስኪ የቃላት ድምጾችን እንቀላቅል

- ለልጅዎ **እስኪ ቃላትን እንቀላቅል! የዚህን ቃል መጀመሪያና ቀሪ ድምጾች እቀላቅላለሁ፤ P-ig, p-ig** ብለው ይነገሩት። ሁለቱን ክፍሎች አንድ ላይ በሚቀላቅሉበት ወቅት በፍጥነት ይድገሙለት። **P-ig, pig። ሞክር፣ p-ig, pig!** ይበሉት
- ከዚያም **አሁን ያንተ ተራ ነው!** ይበሉት። ልጅዎን r-un (run), h-op (hop), እና c-at (cat) የሚሉትን ቃላት እንዲቀላቅል ያድርጉ።

## የጆርናል ሙከራ፥ ጠፈር

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከለሮች፣ እርሳስ፣ የጠፈር የጆርናል ገጽ፣** [*A Voyage to Space/ወደ ጠፈር የሚደረግ ጉዞ*]

- ከልጅዎ ጋር በመንኮራኩር ወደ ጠፈር መጓዝ ምን ሊመስል እንደሚችል በተመለከተ ተነጋገሩ። ልጅዎን *ወደ ጠፈር የሚደረግ ጉዞን* እንዲመለከት ሊመሩት የችላሉ።
- ልጅዎን ስለዚህ እንዲጽፍና እንዲስል ያድርጉ።
- ከዚያም **እስኪ በመንኮራኩር ወደ ጠፈር ስለምታደርገው ጉዞ ንገረኝ! ጠፈር ላይ ምን ታደርጋለህ?** ብለው ይጠይቁት


ስም፥ ________________

በጠፈር መንኮራኩር ውስጥ ወደጠፈር ስላደረጋችሁት ጉዞ ጻፉ፣ ስዕልም ሳሉ።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።






©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም፥ ________________

በጠፈር መንኮራኩር ውስጥ ወደጠፈር ስላደረጋችሁት ጉዞ ጻፉ፣ ስዕልም ሳሉ።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ



## STEM: የቁጥር ካርዶቹን ፈልግ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከ0-10 የቁጥር ካርዶች፣ ቁርጥራጭ ወረቀት ወይም ጋዜጣ፣ የእቃ መያዣ፣ *በአማራጭነት - መቆንጠጫዎች፣ የልብስ መርፌዎች ወይም ረጅም ማንኪያ***

- ለልጅዎ **እስኪ ቁጥሮችን እንመልከት!** ብለው ይንገሩት። ልጅዎን ወረቀት በትናንሽ ክፍሎች እንዲቆራርጥ እና የእቃ መያዣ ውስጥ እንዲያስቀምጣቸው ያድርጉ። የቁጥር ካርዶቹን በሚከቱበት ወቅት በስም እየጠሩ በእቃ መያዣው ውስጥ ይጨምሯቸው።
- ልጅዎን የቁጥር ካርዶችን በስም እየጠራ ለመፈለግ መቆንጠጫዎች፣ የልብስ መርፌ ወይም ረጅም ማንኪያ እንዲጠቀም ይፍቀዱለት።
- *በአማራጭነት - ልጅዎ ቁጥሮችን በሚፈልግበት ወቅት ሊጸፍ ወይም ለመፈተን እርስዎ ከ11-15 የቁጥር ካርዶች ሊጨምሩ ይችላሉ።*

## በግል መማር፥ ጥቃቅን ኮከቦች መሳል

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ወረቀት፣ ውሀማ ቀለም ጥቅል፣ *A Voyage to Space/ ወደ ጠፈር የሚደረግ ጉዞ፣* ለወረቀት ትሪ ወይም ጋዜጣ**

- *ወደ ጠፈር የሚደረግ ጉዞ* መጽሀፍ ገጽ 21ን ተመልከቱ። ከልጅዎ ጋር ስለ ስዕሉ እና ጥቃቅን ነጥቦች እንዴት ጠፈር ላይ ኮከቦች እንደሚሆኑ ተነጋገሩ።
- ልጅዎን በመጀመሪያ ጥቁር ቀለም በመቀባት እና ቀጥሎም ጥቃቅን ነጭ ኮከቦች በመጨመር የጠፈር ስዕል እንዲስል ያድርጉ። ነጭ ነጠብጣቦቹን ለመሳል እንዴት የቀለም መቀቢያ ቡርሹን እንደሚጠቀም በምሳሌ ያሳዩት።




የጠፈር የውጭኛው ክፍል በዙሪያችን ሲሰፋ እያየሁ ነው። በዘመናችሁ ለመቁጠር ከምትችሉት በላይ የበለጠ ደማቅ፣ የሚያብረቀርቁ በርካታ ኮኮቦች አሉ።



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ

PK3 ክፍል 10 ሳምንት 3 ቀን 13

## እውቀት፦ ለራሳችንና ለሌሎች ሰዎች ዘብ መቆም

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፦ ወረቀት፣ ከለሮች፣** *በአማራጭነት - በቀን 7 የተሰሩ -* *Friends Puppets/ የጓደኛሞች አሻንጉሊት ውሾች*




- ለልጅዎ **የሆነ ሰው እኛን ወይም ሌሎች ሰዎችን የሚፈልግ ከሆነ ለራሳችን እና ለሌሎች ሰዎች ለመቆም ቃላት መጠቀም እንችላለን። ይህን ልታቆም ትችላለህ፣ አይሆንም ወይም ይህን አልወደድኩትም ብለን ልንናገር እንችላለን** ብለው ይንገሩት። **ሌላ ምን ልትናገር ትችላለህ?** ብለው ይጠይቁት
- ልጅዎ እራሱን ወይም ሌላ ሰው ደግፎ ስለመቆም ሊስልና ሊጽፍ ወይም ይህን በአሻንጉሊት ውሾቹ አስመስሎ ሊተውን ይችላል።
- ከዚያም **እስኪ ስለ ስዕልህ ንገረኝ! ማንን ደግፈህ ነው የቆምከው?** ብለው ይጠይቁት።

## ያንብቡ፦ *ወደ ጠፈር የሚደረግ ጉዞ*

ኬቲ ሲቪንስኪ
ሰዐሊ፦ ጆይስ ዩ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፦** *A Voyage to Space/ ወደ ጠፈር የሚደረግ ጉዞ*




ወደ ጠፈር የሚደረግ ጉዞ

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆናችሁ አንብቡ። ልጅዎን እየተጓዘ ከገጽ 13 ላይ እንዲቆጥር ያድርጉ!
- ከዚያም **የጠፈር ተመራማሪዎች ወደ ጠፈር ጉዞ ከማድረጋቸው በፊት ምን መማር አለባቸው ብለህ ታስባለህ?** ብለው ይጠይቁት።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ



## እስኪ እንንቀሳቀስ፥ የጠፈር ተመራማሪ ስልጠና

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** ***በአማራጭነት - ሙዚቃ፣ ከ0-10 የቁጥር ካርዶች***

- ለልጅዎ **የጠፈር ተመራማሪዎች ወደ ጠፈር ከመሄዳቸው በፊት ልምምድ ማድረግና ስልጠና መውሰድ አለባቸው። እስኪ እንደ ጠፈር ተመራማሪዎች አስመስለን እንለማመድ** ብለው ይንገሩት።
- እስስ 5 ጃኮች መዝለል፣ 3 ቁጢጥ ማለት፣ 10 መዟዟር፣ ወዘተ ሙከራዎች አስተያየቶች ለመስጠት ተራ ተቀያየሩ።
- *በአማራጭነት - ምን ያክል ሙከራዎች እንደምትሰሩ ለመወሰን በጥቅሉ የቁጥር ካርዶች ያንሱ።*

## አንድ ላይ ሆኖ መማር፥ አየር ላይ እና የጠፈር ሙዚየም

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ የልጅዎን እንደ የከዋክብት ህብር፣ ጨረቃ እና የጸሀይ ስርአት የመሳሰሉ የሳምንት 1 እና 2 ስራዎች ለእይታ ያስቀምጡ፣** ***በአማራጭነት - ከጥቅል ሶፍት የተሰራ ቴሌስኮፕ የመሳሰሉ ተጨማሪ ቁሶች ያዘጋጁ***

- ለልጅዎ **የአየር ላይና የጠፈር ላይ ሙዚየም ስለ ጠፈር የተመለከተ መረጃና ምስሎች ይይዛሉ። አንዳንድ ጊዜ ከዋክብትን የሚያዩባቸው ቴሌስኮፖች ይኖሯቸዋል። ቴሌስኮፖቹ ኮከቦችን አተልቀው የሚየሳዩ ትልቅ አጉዪ መነጽሮችን ይመስላሉ!** ብለው ይንገሩት።
- በጋራ ማመን ጨዋታ ተጫወቱ! በአየርና የተፈር ሙዚየም ላይ እንዳላችሁ አስመስላችሁ ተውኑ። የሙዚየም ጎብኚዎች ወይም ስለ ጠፈር የምታጠኑ የጠፈር ተመራማሪዎች እንደሆናችሁ አስመስላችሁ ልትተውኑ ትችላላችሁ።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሃሙስ

PK3 ክፍል 10 ሳምንት 3 ቀን 14

## **STEM:** የመሬት ስበት


**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከላይ ወደ ታች የሚጣሉ የተለያዩ ቁሳቁሶች፤ ለምሳሌ፡ ኳስ፣ ኩባያ፣ ቀላል ልብስ ወይም ስካርፍ፣ ላባ፣ የጥጥ ኳስ፣ ወዘተ**

- 2 ቁሶች በተመሳሳይ ጊዜ ከላይ ወደ ታች ይወርውሩ። ከዚያም ልጅዎን **ምን ተከሰተ?** ብለው ይጠይቁት
- ከዚያም **ሁለቱም የመሬት ስበት ስለሚስባቸው ተመልሰው መሬት ላይ ወድቀዋል። የመሬት ስበት ነገሮችን ወደ መሬት የሚስብ ሀይል ነው** ብለው ይንገሩት።
- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆናችሁ ስለ ስበት ተመራመሩ። ልጅዎን 2 ቁሶች ከላይ ወደ ታች እንዲጥል ያድርጉ። ተመልከቱና የትኛው ቁስ መጀመሪያ መሬት ላይ እንደወደቀ እና ወይም ሁለቱም አንድ ላይ መሬት ላይ እንደደረሱ ተነጋገሩ። ምርምራችሁን የተለዩ ቁሶችና የተለያዩ ከፍታዎችን በመጠቀም ደግማችሁ

ፍንጭ: ሁለት ቁሶች በተመሳሳይ ፍጥነት መሬት ላይ የማይወድቁ ከሆነ ምክንያቱ አየር በእንቅስቃሴያቸው ላይ በሚፈጥረው ተጽእኖ ነው። ቁሶቹ ጨረቃ ላይ ስበት ስለሌለ በተመሳሳይ ጊዜ ይወድቃሉ!

## በግል መማር፥ የጠፈር ላይ የእግር ጉዞ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** [Space Walk/ የጠፈር ላይ የእግር ጉዞ]()**፣ ከለሮች፣ ለህጻናት ተስማሚ መቀሶች፣** *[Counting to 20 in Space/ ጠፈር ላይ እስከ 20 መቁጠር]()*



- ከልጅዎ ጋር ሆነው ስለ ጠፈር ላይ የእግር ሽርሽር ይነጋገሩ። **አንዳንድ ጊዜ የጠፈር ተመራማሪዎች እንደ ሳተላይት የመሳሰሉ ነገሮችን ለማስተካከል ወይም ምርመር ለማድረግ ከመንኮራኩራቸው ውስጥ ይወጣሉ** ብለው ይንገሩት። በጠፈር ላይ የእግር ሽርሽር ማድረግን ከበጠፈር ላይ እስከ 20 መቁጠር ገጽ 20-21 ላይ ተመልከቱ።
- ልጅዎን ስዕሎቹን ቀለም እንዲቀባና ቆርጦ እንያወጣ ይፍቀዱለት። ስዕሎቹን እራሳቸውን ችለው እንዲቆሙ ይጠፏው። ልጅዎ ስለተለያዩ ኩነቶች ሊጫወትና ሊተውን ይችላል።
- ቀጥለውም **እስኪ ስለ የጠፈር ላይ የእግር ሽርሽርህ ንገረኝ፤ ምን አደረግክ? ምን አየህ?** ብለው ይጠይቁት



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሃሙስ

PK3 ክፍል 10 ሳምንት 3 ቀን 14

## እውቀት፥ ተናገረው

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ በቀን 7 የተሰሩ** [Friends Puppets/ የጓደኛሞች የውሻ አሻንጉሊቶች]



- ለልጅዎ **አንዳንድ ጊዜያት ችግር ሲያጋጥመን ችግሩን አውጥተን ልንናገረው እንችላለን። እርስ በርሳችን ምን እንደሚሰማን ተነጋግረን መፍትሄ ልንፈልግ እንችላለን** ብለው ይንገሩት።
- የአሻጉሊት ውሾቹን ስለ መናገር ለመለማመድ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። የሆነን ሰው የመቆጣት ስሜት ወይም በእት/ወንድማማቾች ወይም ጓደኞች መካከል የሚፈጠር አለመግባባትን አስመስላችሁ ሚና ተጫወቱ።


## የጆርናል ሙከራ፥ የጠፈር ተመራማሪ


**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከለሮች፣ እርሳስ፣ የጠፈር ተመራማሪ የጆርናል ገጽ**






- ከልጅዎ ጋር የጠፈር ተመራማሪዎች ስለሚሰሩት ስራ ተነጋገሩ። የጠፈር ተመራማሪዎች በጠፈር ላይ ስለሚገኙ እንደ ፕላኔቶችና ኮከቦች ስለመሳሰሉ ነገሮች ለማጥናት ወደ ጠፈር ይሄዳሉ። የጠፈር ተመራማሪዎች የጠፈር ላይ የእግር ሽርሽር ያደርጋሉ።
- ልጅዎን የጠፈር ተመራማሪ ስለመሆን እንዲጽፍና እንዲስል ያድርጉ።
- ከዚያም **የጠፈር ተመራማሪ መሆን ትፈልጋለህ? ለምን ወይም ካልሆነም ለምን?** ብለው ይጠይቁት



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።















©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም፥ ________________

የጠፈር ተመራማሪ መሆን ትፈልጋላችሁ? ለምን መሆን ፈለጋችሁ ወይስ ለምን መሆን አትፈልጉም?


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# አርብ



## STEM: ስንት ቁሶች አሉ


**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ እንደ የወረቀት መቆንጠጫዎች ወይም ጠጠሮች የመሳሰሉ በቤት ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶች (20)**

- ለልጅዎ 10 የወረቀት መቆንጠጫዎች ያሳዩት። ከዚያም **ስንት ናቸው?** ብለው ይጠይቁት። የወረቀት መቆንጠጫውን ጠቁመው በሚያሳዩበት ወቅት አብራችሁ ቁጠሩ። ድምሩን ደግመው ይንገሩት። **10 የወረቀት መቆንጠጫዎች አሉ!** ይበሉት።
- ልጅዎን በ10 የወረቀት መቆንጠጫዎች የተለያዩ ስብስቦችን እንዲያዛምድ ይጠይቁት።
- ሙከራውን ከ0 እስከ 10 ባሉት ቁጥሮች መካከል ከ2-3 ተጨማሪ ጊዜያት ደግማችሁ ስሩ። ልጅዎ ስብስብ ሊያሳይዎ እና እርስዎ እንዲቆጥሩ ሊጠይቅዎ ይችላል።

## በግል መማር፥ የጠፈር ላይ ልብሴ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** [Space Suit/የጠፈር ላይ ልብስ](), [*A Voyage to Space/ ወደ ጠፈር የሚደረግ ጉዞ*](), **ከለሮች፣ ውህማ ቀለም ጥቅል፣ ለህጻናት ተስማሚ መቀሶች፣ *በአማራጭነት - እንደ ቁልፎች፣ የተጣጠፈ ወረቀት የመሳሰሉ የማስዋቢያ ቁሶች***

- ከልጅዎ ጋር ስለ የጠፈር አለባበሶች እና እነዚህ ለምን ለጠፈር ተመራማሪዎች አስፈላጊ እንደሆኑ ተነጋገሩ። *ወደ ጠፈር የሚደረግ ጉዞን* ልትመለከቱ ትችላላችሁ።
- ልጅዎን በወረቀት ላይ የጠፈር ልብስ ዲዛይን እንዲያዘጋጅ ወይም የቀረበለትን ስዕል በመቀባትና ቁሶች በመጨመር እንዲያስውብ ያድርጉ።
- ከዚያም **የጠፈር ልብስህ ልዩ ነገር ምንድን ነው?** ብለው ይጠይቁት




©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# አርብ



## እውቀት፥ እስኪ ስለ ጠፈር ተመራማሪዎች እንነጋገር


- ልጅዎን **የጠፈር ተመራማሪ መሆንና ወደ ጠፈር መጓዝ ምን ሊመስል ይችላል ብለህ ታስባለህ?** ብለው ይጠይቁት።
- ልጅዎን ከ2-3 የክትትል ጥያቄዎች ይጠይቁት።- **የጠፈር ተመራማሪ መሆን ትፈልጋለህ? ለምን ወይም ካልሆነም ለምን?** ወይም **የጠፈር ተመራማሪ ብትሆን ምን ማድረግ ትፈልጋለህ? ወደ የትኞቹ ፕላኔቶች መሄድ ትፈልጋለህ?** ብለው ይጠይቁት። የሀሳብ መለዋወጫ ውይይት ለማድረግ ሞክሩ።

## *ያንብቡ፥ ወደ ጠፈር የሚደረግ ጉዞ*

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** *A Voyage to Space/ ወደ ጠፈር የሚደረግ ጉዞ*


- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው መጽሀፉን ያንብቡ።
- ገጽ 18-19ን ያሳዩት እና **አነስተኛ የመሬት ስበት ማጋጠምና ወደ ላይ መንሳፈፍ ምን ይመስላል ብለህ ታስባለህ? ይህን መሞከር ትፈልጋለህ? ለምን ወይም ካልሆነም ለምን?** ብለው ይጠይቁት

ኬቲ ሲቪንስኪ
ሰዐሊ፥ ጆይስ ዩ




ወደ ጠፈር የሚደረግ ጉዞ


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።




©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

የጠፈር ልብስ (FE)


# ሳምንት 4


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# የPK3 ክፍል 10 ሳምንት 4 ጠቅላላ ምልከታ

## ጥላዎች

### በዚህ ሳምንት ልጅዎ፥



በዚህ ሳምንት ልጅዎ ስለ ብርሀን እና እንደ ጥላዎችና ነጸብራቆች ስለመሳሰሉ ከብርሀን ጋር ተያያዥነት ስላላቸው ነገሮች ይማራል። ልጅዎ በተጨመሪም በጥላዎችና ነጸብራቆች አርር ይሰራል፣ የቃላት ክፍሎችን ይቀላቅላል፣ ስለ ማቻቻል በተመለከተ ይማራል እንዲሁም እስከ 10 ቁሶች ይቆጥራል። በቤት ውስጥ የኮከብ ጥላ ለመስራት በጨለማ ክፍል ውስጥ ባትሪ ካላንደር ላይ በማብራት ወይም የሰሜን ብርሀኖችን ለመኮረጅ በባትሪ ላይ ብርሀን የሚያሳልፍ ቀለም የተቀባ ወረቀት ከባትሪ በላይ በማድረግ ቀላል ምርምሮችን ልትሰሩ ትችላላችሁ።

### ቁልፍ ቃላት



## የመሬት ስበት

አንድን ነገር መሬት ላይ እንዲወድቅ የያደርግ ወይም ወደ ሌላ ፕላኔት እንዲሳብ የሚያደርግ ሀይል ነው።



## ነፀብራቅ

በመስታወት፣ ብርጭቆ ወይም ውሀ ውስጥ የምናየው ምስል ነው



## ጥላ

የሆነ ሰው ወይም የሆነ ነገር በወለልና ብርሀን መካከል በሚቆምበት ወቅት የሚፈጠር ጥቁር ምስል ነው


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ግንኙነቶችን ይፍጠሩ

ይህ በጠፈር ላይ ክፍላችን የመጨረሻው ክፍል ነው። መርሀግብሩን ከመጀመርዎ በፊት እስካሁን ከተማሩት ትምህርት ውስጥ ስላስደሰተዎ ነገር በተመለከተ ይጻፉ እንዲሁም ይሳሉ።

ያስቡበት!


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሰኞ



## **STEM:** የተወርዋሪ ኮከብ መቆም ዳንስ


**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ወረቀት፣ እርሳስ፣ ሙዚቃ፣ ከ0-10 የቁጥር ካርዶች**

- የቁጥር ካርዶችን ወለል ላይ የተለያዩ ቦታዎች ያስቀምጠዋቸው። ከልጅዎ ጋር ወለል ላይ ያሉትን ቁጥሮች በጋራ ጥሩ።
- ለልጅዎ **ሙዚቃው በሚጫወትበት ወቅት ልትደንስ ትችላለህ። በጠፈር ላይ እንደሚበር ተወረዋሪ ኮከብ አስመስለህ ተውን። እኔ ቁጥር እጠራልሀለሁ። ወለል ላይ ወዳለው ቁጥር ልክ እንደተወርዋሪ ኮከብ አስመስለህ ብረርና ቁጥሩ ላይ ቁምበት** ብለው ይንገሩት።
- ጥቂት ዙሮችን ተጫወቱ። ከዚያም ልጅዎን እንዲመራና እርስዎ የሚፈልጉትን ቁጥር እንዲጠራልዎ ይፍቀዱለት።
- በተጨማሪም በዜሮ የመሬት ስበት ላይ እንደሚራመደዱ የጠፈር ተመራማሪዎች ወይም በጸሀይ ዙሪያ እንደሚዞሩ ፕላኔቶች አስመስላችሁ ልትተውኑ ትችላላችሁ።

## በግል መማር፦ የፀሀይ መውጫ አርት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡** ***A Voyage to Space/ወደ ጠፈር የሚደረግ ጉዞ፣*** **ውሀማ ቀለም ጥቅል፣ ወረቀት፣ *በአማራጭነት - ማጣበቂ፣ የተቀለሙ የልብስ ሽንተረሮች ወይም ወረቀት፣ መጽሄቶች ወይም ፎይል***

- ከልጅዎ ጋር ከገጽ 8-9 ላይ ስለ ፀሀይ መውጫ ተነጋገሩ። ከዚያም **ሰዐሊው ስዕሉን እንዴት እንደሳለው በተመለከተ ምን ታያለህ do?** ብለው ይጠይቁት። ስለ የተለያዩ ሽንተረር ቅቦች ወይም የጸሀይ መውጫን ለመስራት ቀለሞች ስለመቀባት ተነጋገሩ።
- ልጅዎን ቀለም ወይም የልብስ ሽንተረሮች ወይም የተቀባ ወረቀት በመጠቀም የጸሀይ መውጫ ስዕል እንዲስል ያድርጉ።
- ከዚም **እስኪ ስለ ስዕልህ ንገረኝ። ለጸሀይ መውጫህ ምን አይነት ቀለም ተጠቀምክ?** ብለው ይጠይቁት





ወደ መላኪያው ቦታ መንዳት፣ ጸሃዩዋ ከአማስ ስትወጣ አያታለሁ። ጥቁሩ ሰማይ ወደግራጫ ይቀየራል፣ ከዛም ወደሚያምር ፒንክ ቀለም ይቀየርና በመጨረሻም፣ ብርሃን ይወጣል። ጸሃዩዋ ከጠፈር ላይ ስትታይ ምን እንደምትመስል ሳስበው ይገርመኛል።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሰኞ



## እውቀት፥ ማቻቻል




"ግቡ፣" አለች ኤንጅል፣ "ግቡ ሁለታችንም ደስ እንዲለን ከሆነ፣ እስካሁን ድረስ ምን ማድረግ እንደነበረብኝ ማወቅ ነበረብኝ። መጋራትን እየተማርን ሁለታችንም እንድንዝናና፣ ከበዲ ዘ ቤር ጋር በየተራ መጫወት አለብን።"

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ወረቀት፣ ከለሮች,** ***በአማራጭነት - ቀደም ሲል የተሰሩት*** *Friends Puppets/የጓደኛሞች አሻጉሊት ውሾች፣ Buddy the Bear/በዲ ዘ ቤር*


- ለልጅዎ **ችግራችንን እንዴት እንደምንፈታ ስንነጋገር ቆይተናል። አንደኛው መንገድ ማቻቻል ነው። ሁለት ሰዎች በሚያቻችሉበት ወቅት ሁለቱም የሚፈልጉትን ነገር በጥቂቱ ያቻችሉና ሁለቱም ደስተኛ ይሆናሉ** ብለው ይንገሩት። ምሳሌዎች ይስጡት፤ ለምሳሌ፡ ጌም በምትጫወቱበት ወቅት ሁለታችሁም መጀመሪያ መጀመር የምትፈልጉ ከሆነ ተራችሁን መጠበቅ

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው የቤት ውሾቹን በመጠቀም ስለ ማቻቻል አስመስላችሁ ተውኑ! ሙከራውን በቤት ውስጥ እንደ አንድ አይነት አሻጉሊቶ መፈለግ የመሳሰሉ ኩነቶችን በመጠቀም ደጋግማችሁ ስሩ።
- *በአማራጭነት - ድቡ በዲ የሚለውን ምንባብ አንብቡ። ስለ ገጽ 20-25 ተነጋገሩ እና* ***ኤንጅልና ብሪ አቻችለዋል። ሁለቱም ከበዲ ጋር መጫወት ፈልገው የነበረ ቢሆንም ተራ ለመጠበቅና አብረው ለመጫወት ወስነዋል*** ብለው ይንገሩት።

በተጨማሪም *የድቡ በዲ/ Buddy the Bear* በቅድሚያ በድምጽ የተቀዳ ምንባብን ከSparkler መተግበሪያ ላይ "ለአዋቂዎች የቀረቡ ፍንጮች" ጠየናማ ሰውነቶች፣ ጤናማ አእምሮዎች ክፍል ስር ማግኘት ይችላሉ።

## ያንብቡ፥ ኮዮቴና ጥንቸል

ኮዮቴና ጥንቸል




**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** *Coyote and Rabbit/ኮዮቴና ጥንቸል*

- ከልጅዎ ጋር ሆነው መጽሀፉን ያንብቡ።
- **ኮዮቴ በጥንቸሉ እጅግ ተናዶ ነበር። ከዚህ በፊት ተናደህ ታውቃለህ? ስትናደድ ሰውነትህን ምን አይነት ስሜትና ገጽታ ተሰማህ?** ብለው ይጠይቁት። ከልጅዎ ጋር ንዴቱን እንዴት መግለጽ ስለሚችልባቸው መንገዶች ተነጋገሩ። ፊቱ ፈገግታ ያጣል፣ ሰውነቱን ከባድ ስሜት ይሰማዋል ወይም የልብ ምቱ ሊፈጥን ይችላል።

በተጨማሪም የመጽሀፉን በቅድሚያ በድምጽ የተቀዱ ምንባቦችን ከSparkler መተግበሪያ ላይ "ለአዋቂዎች የቀረቡ ፍንጮች" ወደ ጠፈር መጓዝ ክፍል ስር ማግኘት ይችላሉ!ce!



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ማክሰኞ

PK3 ክፍል 10 ሳምንት 4 ቀን 17

## STEM: ጥላዎች


**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** Hand Shadows/የእጅ ጥላዎች, **መብራት ወይም ባትሪ**



- ባትሪ ወይም መብራት የምትጠቀሙ ከሆነ ወደ ጨለማ ክፍል ሂዱ፤ ወይም ወደ ውጭ ውጡና ጥላዎች ለመስራት የጸሀይ ብርሀን ተጠቀሙ።
- **ጥላ የሆነ ነገር ብርሀንን ሲጋርድ ይፈጠራል** ብለው ይንገሩት። ጥላ እንዴት እንደሚሰራ ያሳዩት። ልጅዎን በእጆቹ ጥላ እንዲሰራ እና ምን እንዳየ እንዲያብራራ ያበረታቱት። ጥላው በእጁ የሚሰራው ነገር ነው።
- ልጅዎን ወደ ብርሀን እንደሚርቅበት መጠን ላይ ተመስርቶ ትልቅ ወይም ትንሽ ጥላ በመፍጠር ጥላዎች ሰለመስራት እንዲመራመር ያድርጉ።
- ልጅዎ ጥላዎችን በስዕሎች ሊሰራ ወይም የራሱን ምስሎች ሊሰራ ይችላል።

## በግል መማር፥ እርዳታ መጠየቅ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ በቀን 7 የተሰሩ** Friends Puppets/የጓደኛሞች አሻንጉሊት ውሾች



- ለልጅዎ **አንዳንድ ጊዜ ልንናደድና ለንበሳጭ እና እንዴት እንደምንረጋ ላናውቅ እንችላለን። በዚህ ጊዜ አብሮ አደግ ጓደኞችን ሊረዳን ይችላል!** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን እርዳታ ማግኘት ስለፈለገበት ጊዜ እንዲያስብ ያድርጉት። ከዚያም **እርዳታ ዩጠየቅከው እንዴት ነበር? ማን እርዳታ አደረገልህ?** ብለው ይጠይቁት።
- ለልጅዎ የቤት ውሾቹን በመጠቀም እርዳታ ስለመጠየቅ እንዲለማመድ ይፍቀዱለት።
- ከዚያም **እስኪ ውሾቹ እንዴት እርዳታ እንደጠየቁ አሳየኝ። ሌሎች ይህን እርዳታ ጠይቀዋል?** ብለው ይጠይቁት።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ማክሰኞ



## እውቀት፥ እስኪ ስለዚህ ንገረኝ

- ለልጅዎ **በዚህ ሳምንት ስለ ጠፈር እንነጋገራለን እንዲሁም ስለ ብርሀን እንማራለን። እንደ እስሳት ስለመሳሰሉ ከተፈጥሮ የምናገኛቸው ብርሀኖች እና እንደ አምፑል ስላሉ ሰው ሰራሽ ብርሀኖች በተመለከተ እንማራለን** ብለው ይንገሩት።
- ከዚያም **ስለ ምን መማር ትፈልጋለህ? ለምን? ተጨማሪ መረጃ ከየት ማግኘት እንችላለን?** ብለው ይጠይቁት።

## የጆርናል ሙከራ፥ ጥላዬ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከለሮች፣ እርሳስ፣ የጥላዬ የጆርናል ገጽ**

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ስለ ጥላዎች ተነጋገሩ። በክፍል ውስጥ ጥላ የሰሩ ቁሶችን ጠቁመው ያሳዩት።
- ልጅዎን የራሱን ስዕልና የራሱን ጥላ እንዲስል ያበረታቱት።
- ከዚያም **በስዕልህ ላይ ምን አደረግክ? ጥላህ የት አለ? ጥላህ አንተ የምታደርገውን ነገር ያደርጋል?** ብለው ይጠይቁት።


ስም፥ ________________

የራሳችሁን እና የጥላችሁን ስዕል ሳሉ።



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።



**ሸርጣን**



**ውሻ**



**ዝሆን**



**ሙስ**



**ወፍ**



**ቀንድ አውጣ**


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።


ስም፥ ________________

የራሳችሁን እና የጥላችሁን ስዕል ሳሉ።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

## STEM: የተወርዋሪ ኮከቦች ስብስቦች

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ Comet Sets/ የተወርዋሪ ኮከቦች ስብስቦች፣ ከለሮች፣ ለህጻናት ተስማሚ መቀሶች፣ ከ0-10 የቁጥር ካርዶች**




- ልጅዎን ተወርዋሪ ኮከቦቹን እንዲቆጥራቸውና ቀለም እንዲቀባቸው ከዚያም ቆርጦ እንዲያወጣቸው ያድርጉ።
- 6 ተወርዋሪ ኮከቦች ያስቀምጡና ልጅዎን እንዲቆጥራቸው እና ከዚያም ከብዛታቸው ጋር ተመሳሳይ የቁጥር ካርድ (8) እንዲፈልግ ይጠይቁት።
- ሙከራውን በተለያዩ መጠኖች ደጋግማችሁ ስሩ
- *በአማራጭነት - ልጅዎ ቁጥር ሊመርጥና የተወርዋሪ ኮከቦች ስብስብ ሊሰራ ይችላል። ብዙ ጊዜ ደጋግማችሁ ስሩ።*

የቁጥር ካርዶቹን በዚህ ክፍል ውስጥ በሙሉ ለመጠቀም ያስቀምጧቸው።

## በግል መማር፥ የመብራት መገጣጠም

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ Light Puzzle/የመብራት መገጣጠም, ከለሮች፣ ለህጻት ተስማሚ መቀሶች፣ *በአማራጭነት - ቁርጥራጮቹን ቀለም ከመቀባትዎና ቆርጠው ከማውጣትዎ በፊት***




- በመጋጠጠሙ ላይ ስለተለያዩ የብርሀን ምንጮች ተነጋገሩ። ከዚያም **ሁለት አይነት ብርሀኖች አሉ - ከተፈጥሮ የምናገኘው ብርሀን እና ሰው ሰራሽ ብርሀን** ብለው ይንገሩት። እንደ እሳት፣ ጨረቃ እና ከዋክብት ስለመሳሰሉ የየተፈጥሮ ብርሀኖች እና እንደ የመንገድ መብራትና የቤት ውስጥ መብራት ስለመሳሰሉ ሰው ሰራሽ የብርሀን ምንጮች ይንገሩት።
- ልጅዎን ቁርጥራጩን ቀለም እንዲቀባና ቆርጦ እንዲያወጣ ያድርጉ። ከዚያም ቁርጥራጮቹን ከ1 እስከ 10 በቅደም ተከተል ቆርጦ እንዲያወጣ ያድርጉ።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ


PK3 **ክፍል** 10 **ሳምንት** 4 **ቀን** 18

## እውቀት፥ የቃላት ድምጾችን መቀላቀል ምልከታ

- ለልጅዎ **እስኪ ቃላትን እንቀላቅል! የዚህን ቃል መጀመሪያና ቀሪ ድምጾች እቀላቅላለሁ፤ J-am, j-am** ብለው ይነገሩት። ሁለቱን ክፍሎች አንድ ላይ በሚቀላቅሉበት ወቅት በፍጥነት ይድገሙለት። **J-am, j-am። ሞክር፣ j-am, jam!** ይበሉት።
- ከዚያም **አሁን ያንተ ተራ ነው!** ይበሉት። ልጅዎን p-ot (pot), c-ap (cap), እና h-ut (hut) የሚሉትን ቃላት እንዲቀላቅል ያድርጉ።

## ያንብቡ፥ ኮዮቴና ጥንቸል

ኮዮቴና ጥንቸል




**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** [*Coyote and Rabbit/ኮዮቴና ጥንቸል*, Stop/አቁም, Think/አስብ, Act/እርምጃ ውሰድ]

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው መጽፉን ያንብቡ።
- የ"ቁም፣ አስብ፣ እርምጃ ውሰድ" ስዕሎች ያሳዩት እና የሚያበሳጨውን ችግር እንዴት እንደሚፈታ በተመለከተ ተነጋገሩ። **ኮዮቴ ተበሳጭቶ ነበር። ሆኖም ለመቆም፣ ለማሰብና እርምጃ ለመውሰድ ወሰነ። አንዳንድ ጊዜ ስንናደድ ለማሰብ ይከብደናል። ጥቂት ትንፋሽ ለመውሰድ ልንቆም፣ ስለ ችግሩ ልናስብ እና አመቺ መፍትሄ ልንፈልግ እንችላለን። ከዚያም እንሞክረዋለን!** ብለው ይንገሩት

በተጨማሪም የመጽሀፉን በቅድሚያ በድምጽ የተቀዱ ምንባቦችን ከSparkler መተግበሪያ ላይ "ለአዋቂዎች የቀረቡ ፍንጮች" ወደ ጠፈር መጓዝ ክፍል ስር ማግኘት ይችላሉ!


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።


## እስኪ እንንቀሳቀስ፥ የጥላ እንቅስቃሴዎች

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** ***በአማራጭነት - ሙዚቃ***

- ለልጅዎ **እስኪ አንዳችን የሌላኛችን ጥላ እንደሆንን አስመስለን እንስራ** ብለው ይንገሩት። ሌላኛው ሰው ጥላ ይሆንና እንቅስቃሴዎችን ይቀዳል።
- መሪ የመሆንና ጥላ የመሆን ተራዎችን ተቀያየሩ።


## አንድ ላይ ሆኖ መማር፥ የጥላ ቲያትር

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** [Hand Shadows/የእጅ ጥላዎች](), **አምፑል ወይም ባትሪ፣ ግድግዳ ያለው ክፍል፣** ***በአማራጭነት - ሳቢ ቅርጽ ያላቸው አሻንጉሊቶች ወይም መደገፊያዎች***





- አምፑል ወይም ባትሪ የምትጠቀሙ ከሆነ ወደ ጨለማ ክፍል ሂዱ ወይም ወደ ውጭ ሂደና ጥላዎች ለመስራት የፀሀይ ብርሀን ተጠቀሙ።
- ከዚያም **እስኪ የጥላ ቲያትር እንስራ! እስኪ በእጆቻችን የተለያዩ እንስሳትን እንስራ** ብለው ይንገሩት። ለልጅዎ እንዴት ጥላ መስራት እንደሚችል ለማሳየት ስዕሎቹን ይጠቀሙ።
- የተለያዩ ገጸ ባህሪያትን በመፍጠር እና በጋራ ትዕይንቱን በመተወን ተዝናኑ!


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።





©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።





©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።






©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሃሙስ

PK3 ክፍል 10 ሳምንት 4 ቀን 19

## STEM: ነፀብራቆች

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከ1-2 መስታወቶች ወይም የራስ ምስልን የሚያነሳ/ሰልፊ ስልክ፣ *በአማራጭነት - እንደ ማንኪያዎች የመሳሰሉ አንፀባራቂ ሽቦዎች ወይም የብርጭቆ ቁሶች ለምሳሌ የውሀ መጠጫ ብርጭቆ (በጥንቃቄ ይቆጣጠሩ)፣ መስኮቶች፣ ውሀ፣ ወዘተ***

- ለልጅዎ **ነፀብራቅ እንደ መስታወት፣ ብርጭቆ ወይም ውሀ በመሳሰሉ ብርሀን አንጸባራቂ ነገሮች ላይ አርፎ ሰመለስ ይፈጠራል** ብለው ይንገሩት። መስታወት ተመልከቱና ምን እንዳያችሁ ያብራሩለት።
- ልጅዎን በመስታወቶች ላይ እንዲመራመር ያበረታቱት። በቁጥር ያልተወሰኑ ምስሎችን ለማግኘት ሁለት መስታወቶችን ትይዩ አስቀምጡና ተመራመሩ። ነጸብራቆችን በውሀ፣ መስታወት፣ መስኮት ወይም አንፀባራቂ መስታወት ውስጥ ለማየት ሞክሩ።

## በግል መማር፥ የምስል ነፀብራቅ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ መስታወት ወይም እራስን ለማንሳት/ሰልፊ የተስተካከለ ስልክ፣ ወረቀት፣ ከለሮች ወይም ውሀማ ቀለም ጥቅል**

- ልጅዎን የራሱን ነጸብራቅ እንዲመለከት እና ነጸብራቁን በመመልከት የራሱን ስዕል እንዲስል ያድርጉ።
- ከዚያም **ነፀብራቅህን በማየት የራስህን ስዕል መሳል ምን ይመስላል? ከባድ ነበር?** ብለው ይጠይቁት



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሃሙስ

PK3 **ክፍል** 10 **ሳምንት** 4 **ቀን** 19

## እውቀት፥ ለኮዮቴ የሚጻፍ ደብዳቤ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** *Coyote and Rabbit/ኮዮቴና ጥንቸል፣* Stop/አቁም, Think/አስብ, Act/አርምጃ ውሰድ, **ወረቀት፣ ከለሮች**




- ከልጅዎ ጋር ለኮዮቴ ችግሩን እንዲፈታ መርዳት ቢችል ምን ብሎ እንደሚነግረው ተነጋገሩ።
- ልጅዎን ለኮዮቴ የችግሩን መፍትሄ አስመልክቶ ደብዳቤ እንዲጽፍለት ያድርጉ።
- ከዚያም **በደብዳቤህ ላይ ለኮዮቴ ምን መፍትሄ ሰጠኸው?** ብለው ይጠይቁት

## የጆርናል ሙከራ፥ የመሬት ስበት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከለሮች፣ እርሳስ፣ የመሬት ስበት የጆርናል ገጽ፣** *A Voyage to Space/ወደ ጠፈር የሚደረግ ጉዞ*




- ለልጅዎ **የመሬት ስበት ምድር ላይ እንድንቆይና በዙሪያዋ እንድንንሳፈፍ ይረዳናል** ብለው ይንገሩት። ለልጅዎ አነስተኛ የመሬት ስበት ሲኖር ምን እንደሚመስል ለማሳየት *ወደ ጠፈር የሚደረግ ጉዞን* ገጽ 19 ያሳዩት።
- ልጅዎን ጥቂት የመሬት ስበት ሲኖር ወይም ምንም የመሬት ስበት ሳይኖር ምን እንደሚመስል በተመለከተ እንዲጽፍ እና እንዲስል ያድርጉ።
- ከዚያም **የመሬት ስበት በሌለበት ቦታ መኖር ምን ይመስላል ብለህ ታስባለህ? ምንም የመሬት ስበት ባይኖር ምን ታደርጋለህ?** ብለው ይጠይቁት



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም፥ ________________

የመሬት ስበት ቦታ ላይ መሆን ምን አይነት ነገር ይፈጥራል?


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# አርብ

PK3 ክፍል 10 ሳምንት 4 ቀን 20

## STEM: ስንት ጣቶች አሉ?

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** ***በአማራጭነት - ከ0-10 የቁጥር ካርዶች***

- ለልጅዎ 7 ጣቶችዎን ያሳዩት። ከዚያም **ስንት ጣቶች አሉ?** ብለው ይጠይቁት። እያንዳንዱን ጣቶች ከግራ ወደ ቀኝ በሚያንቀሳቅሱበት ወቅት አብራችሁ ቁጠሩ (ለልጅዎ ምልከታ)። ድምሩን መልሰው ይንገሩት። **7 ጣቶች አሉ!**
- ልጅዎን 7 ጣቶች እንዲያሳይ ይጠይቁት።
- ሙከራውን ከ0 እስከ 10 መካከል ባሉ ቁጥሮች ከ2-3 ተጨማሪ ጊዜያት ደግማችሁ ስሩ። በተጨማሪም ልጅዎ ስብስብ ሊያሳይዎ እና እርስዎ ሊቆጥሩ ይችላሉ።
- ለመፈተን ለልጅዎ ጣቶችዎን ያሳዩት እና በቤትዎ ውስጥ ተመሳሳይ ቁጥር ያላቸው ቁሶችን እንዲፈልግ ያድርጉት።

## በግል መማር፥ “ወደ ጠፈር መጓዝ”ን መሰናበት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ወረቀት፣ ከለሮች**

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ስለ ጠፈር፣ የኮከብ አጥኚዎችና እና የጠፈር ተመራማሪዎች ከተማረው ትምህርት ውስጥ የትኛውን ክፍል እንደወደደው በተመለከተ ተነጋገሩ። ይህ ተግባር ወይም መጽሀፍ ሊሆን ይችላል።
- ልጅዎን ይህን እንዲጽፍ እና እንዲስል ያድርጉ።
- ከዚያም **የጻፍከው ስለ ምንድን ነው? ይህን የወደድከው ለምንድን ነው?** ብለው ይጠይቁት።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# አርብ



## እውቀት፥ ቃሉን ገምት


- ለልጅዎ **እስኪ ጌም እንጫወት። ስለተማርነው ስለተወሰነ ነገር የተመለከቱ ፍንጮች እሰጥሀለሁ። ከዚያም አንተ ቃሉን ትገምታለህ** ብለው ይንገሩት።
- ከጭብጥ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ቃላት ይጠቀሙ፤ ለምሳሌ፡ ብርሀን በምትጋርዱበት ወቅት የምታዩት ነገር (ጥላ)፣ በመስታወት ስትመለከቱ ምን እንደምታዩ (ነፀብራቅ)፣ ስለ ጠፈር የሚያጠና ሳይንቲስት (የጠፈር ተመራማሪ)
- ልጅዎ እርስዎ የሚገምቱትን ፍንጮች እንዲሰጥዎ ሚናችሁን ተቀያየሩ።

## ያንብቡ፥ *ኮዮቴና ጥንቸል*

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** *Coyote and Rabbit/ኮዮቴና ጥንቸል*, Stop/አቁም Think/አስብ፣ Act/እርምጃ ውሰድ

- ከልጅዎ ጋር ሆነው መጽሀፉን ያንብቡ።
- ለልጅዎ **ኮዮቴ ጥንቸሉን በተመለከተ ትክክለኛውን ውሳኔ ለመወሰን ይቆም፣ ያስብ እና እርምጃ ይወስድ ነበር። እሰኪ ስለ አንድ ችግር እናስብ እና እንዴት መቆም፣ ማሰብ እና እርምጃ መውሰድ እንደምንችል እንነጋገር** ብለው ይንገሩት።
- የቅርብ ችግር ምሳሌ ሊጠቀሙ ይችላሉ፤ ለምሳሌ፡ የወንድም/እህት አሻንጉሊት ነጥቆ መውሰድ


ኮዮቴና ጥንቸል





©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ወደጠፈር መጓዝ ወደተሰኘው ወደ ክፍል 10 እንኳን በደህና መጣችሁ! በክፍል 10 ስር ልጅዎ እንደ የብስ/መሬት፣ ውሃ እና አየር የመሳሰሉት ወደጠፈር ለመጓዝ የሚያስፈልጉ ነገሮች ይማራል።



AppleTree

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።